@bookshelf99

6

ምስጢር የአባቷ ሰባተኛ ሙት አመት የሚዘከረው ቅዳሜ ቢሆንም የሳምንት መጨረሻውን አዲስ አበባ ላለመቆየት ወስናለች ። እናቷን ብቻቸውን ትታ መሄዷ ቅር ቢላትም ፣ የሚሰበሰቡትን ያባቷን ዘመዶች ማየት ስላልፈለገች ሌላ አማራጭ አልታያትም ። እናቷም ብትኖርላቸው ደስ ቢላቸውም ፣ ችግሩን ስለሚያውቁ የግድ ሊሏት አልፈለጉም ። አርብ ማታ ላይ ከአብሮ አደግ የቅርብ ጓደኛዋ ጋር ወደ ደብረዘይት ኩሪፍቱ ተያይዘው ወጡ ።

ቅድሜን ናዝሬት ላይ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር አሳልፈው ከመሸ ወደ ደብረዘይት ተመለሱ ። ደክሟቸው ስለነበር እንደገቡ ነበር የተኙት ። ድምጽ በቀላሉ የሚቀሰቅሳት ምስጢር ሌሊት ላይ ስትነቃ ጓደኛዋ አልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀምጣ እየተንሾካሾከች ታወራለች ። ስልኩን እስክትዘጋ ጠበቀችና "ውይ ምን ይሻልሻል ማርቲ ... ቀይ በቃ አንቺ ከውቂያኖስ ማዶ የሚንተከተክ ፍቅር ይዞሻልና ስው አይተኛበትም እንዴ? አይደክምሽም እንዴ ደግሞ?" አለች ፣ ሙሉ ለሙሉ ያልነቃ ፊቷን እያሻሸችና እየተንጠራራች ።

"በኔ የደረሰው ይድረስብሽ ብዬ ልመርቅሽ?" አለች ፣ ስልኩን መልሳ ኃይል መሙያው ላይ እየሰካች ።

"ኡሁሁ ... ባትሪ እስኪንጠፈጠፍ የሚያስወራ የርቀት ፍቅርስ ይቅርብኝ ... ምርቃቱ ላንቺው ይሁን ። ለመሆኑ ደህና ነው? መቼ ነው የሚመጣው ግን እሱ?" አለች ፣ አልጋው ውስጥ እንዳለች ትራሷን ደራርባ ለመቀመጥ እየተመቻቸች ።

"ምኑ ይታወቃል ብለሽ ነው አሁንስ ... ማስተርሱ ተጠናቀቀ ብዬ ተንፈስ ስል ለፒኤችዲ ስኮላርሺፕ ሰጡኝ ነው የሚለኝ ። እሱን ሳያመቻች ወደ እዚህ ከመጣ ደግሞ ቪዛ ሊከለክሉኝ ይችላል ብሎ ፈራ ። ... አይ ዶኖ ... እንዴት እንደናፈቀኝ ፣ ኡፍ ...ፍ ... አሁንስ ትምህርት የሚባል ነገር ቢጠፋ ምናለ" ብላ ፣ ትራሷን እቅፍ አድርጋ ኩርምት ብላ ተቀመጠች ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አይ ኖው፣ አይዞሽ የኔ ናት። ግን ታዲያ መቼ ነው የሚመጣው? ቀይ ግን እኔ የምልሽ ፒኤችዲውንም የሚሰራው በፊሎሶፊ ነው?"

"መሰለኝ ... ሌላ ምን ይሆናል ብለሽ ነው? አንዴ በርሱ ተለክፏል።" ጣረ ጣራውን እያየች ጣቶቿን ማንቋቋት ጀመረች።

"ከዛስ እዚህ መጥቶ ለማስተማር ነው? ምንድነው ዓላማው?" በጣም ራስ ወዳድ የሆነ ስለመስላት የበለጠ አናደዳት። ብዙ ቀርባ ባታውቀውም ድሮውንም የፍቅር ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ቁም ነገረኛ ነው ብላ አታስብም ነበር። 'ከቀለም የተጋባ፣ በሳምባው ሳይሆን በትምህርት የሚተነፍስ የእድሜ ልክ ተማሪ' አለች በልቧ።

"መፈላሰፍ ነዋ ... እኔ አንትሮፖሎጂ፣ እሱ ፍልሰፍና አጥንተን፣ ልጆቹ ምን እንደሚበሉ ማን ያውቃል?" ብላ፣ እምባዋን ዋጥ አድርጋ የግዷን ሳቀች።

"የምር ግን ማርቲ ለምን የሆነ ሥራ የሚያስገኝ፣ አለ አይደል፣ የሆነ ሙያ ነገር አያጠናም መጀመሪያ? ፍልሰፍናው እንደሆነ የት ይሄድበታል? ሲሪየስሊ፣ ምንድነው ግን ፊዩቸራችሁ?" አለች፣ ሙሉ ለሙሉ ወደ ማርታ ዞራ ለመቀመጥ ትራሷን እያመቻቸች።

"እሱስ ችግር አልነበረውም። ለርሱ ደስ ካለው ይሁን፤ ግን ደግሞ በቃ ... ሁሉም ነገር ቄልም ብሎብኛል። ናፍቆቱም ነው መሰለኝ ..." ብላ፣ ካልጋዋ ላይ ፍንጥር ብላ ተነስታ በባዶ እግሯ ቀንጠር ቀንጠር እያለች ሄዳ የመስኮቱን መጋረጃ ከፈተችው። ሰማዩ ገና መላቀቅ እየጀመረ ነው። "እስኪ እዪው ... ሌሊቱ ይነጋል፣ ደመናውም ዞሮ ዞሮ ሲበቃው ያዘለውን ትነት አቀዝቅዞ ውሃ ያደርገውና ይዘንባል። አበባው ውበቱን አርግፎ ፍሬ ይሆናል። የኔ ህይወት ብቻ ሁሌም ባለህበት እርገጥ ... እንቄቄ እንደሆነ የሚኖረው እስከመቼ ነው?" አለች። መስኮቱን ሙሉ ለሙሉ ስትከፍተው ቀዝቀዛው የማለዳ አየር የጋለ ፊቷን በረድ አደረገላት። ምስጢርም ከአልጋዋ ወርዳ በስስ ፒጃማዋ ላይ የማታ ጋውኗን ደርባ በዝምታ ካጠገቧ ቆመች።

"ይሄም ደግሞ ያልፍና ... እንደገና አብራችሁ ትሆኑና መሳቃችሁ አይቀርም። አይዞሽ" ስትላት፣ ዞር ብላ አቀፈቻትና አንገቷ ስር ገብታ ማልቀስ ጀመረች። "እንዴ! ምነው ማርቲ? ኧረ አይዞሽ" ብላ፣ ጀርባዋን መታ መታ ስታደርጋት ይባስ እየተንሰቀሰቀች

"ትናንትና ማታና ቅድም በጣም ተጨቃጭቀን ነው ስልኩን የዘጋነው። እሱ ሁሉ ነገር ላይ ይፈላሰፋል። ምን ያህል እንደምወደውና እንደምናፍቀው እንኳ የሚገባው አይመስለኝም። ኡፍፍ ... ሰውንም እንደ እቃ ከውስጥሽ አሽቀንጥሮ መወርወርና ትውት ማድረግ ቢቻል እንዴት ጥሩ ነበር" ብላ፣ ስፍራውን ለቀቅ እየለቀቀ ባለው ጨለማ ውስጥ አሻግራ ማየት ጀመረች። እንደ ቀሙ ሲያወሩ ቀዩና የጠዋቱ ብርድ ቅዝቃዜ ሲጠነክርባቸው በሩን ዘግተው በየአልጋቸው ውስጥ ገቡና

Brought to You by t.me/bookshelf99

ወሬያቸውን ቀጠሉ ።

"ቀይ የኔስ አንዴ አዞብኝ ነው ... አንቺ ግን በቃ አሻፈረኝ ማለትሽ ነው?" ስትላት ፣ ስለምን እንደምታወራ ብታውቅም እንዳልገባት ሆና

"ምኑን ነው አሻፈረኝ የምለው ማርቲ?"

"ምን እንዳላወቀ ትሆኖለሽ ... ቀይ መልኩ ብትዪ ... ቁም ነገረኛነቱ ፣ ምን አነሰው ብለሽ ነው? በዚያ ላይ እሱም ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሳይኪያትሪስት ይሆንና አብራችሁ አገሩን እያሳበዳችሁና እያስተባበዳችሁ አሪፍ ኑሮ ትኖሩ ነበር ... ደስ አይልም?" ስትላት ፣ ከት ብላ በረጅሙ ሳቀች ። ምስጢር ከጥቂት ወራት በፊት ጳውሎስ ሆስፒታል የካውንስሊንግ ስይኮሎጂ ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋትን የልምምድ ሥራ ለመሥራት ሄዳ ነበር ። በዛው አጋጣሚ የአእምሮ ሕክምና ጥናት ሠልጣኝ ከሆነው ዶክተር ሲራክ ስር ትሰራ ነበር ። እንዳፈቀራት የነገራትን አጫውታት ነበር ። ካላስተዋወቅሽኝ ብላ ካየችው በኋላ እሺ እንድትለው መሞትሞቷን ቀጥላለች ።

"ቀይ ግን አንቺ እሱ ላይ ምን አይተሻል? ተላክሽ ወይስ ሚስጥር ለእሱ እሺ ካላለች ባል አታገኝም ... ምናምን ተባልሽ?" አለቻት ፣ የታች ከንፈሯን ጠመም ረዘም አድርጋ ትከሻዋን እየሰበቀች ።

"እኔ ለራስሽ ብዬ ነው ... እንደሱ አይነት ቀሽት ወንዶች ከገበያው ላይ እንደ ዋልያ ተመናምነዋል ። ያሉትም ተይዘው በየሴቱ የፍቅር ሙዚየም ገብተው ሳያልቁ አይቀርም ይባላል" ስትል ፣ ሁለቱም እንደ ሞኝ ትራሳቸውን ይዘው በረጅሙ ሳቁ ።

ትንሽ ጋብ ሲልላቸው ፣ "የኔ እህት ... እኔ ካገኘው ሴት ጋር የሚጓተት ወንድ ደስ አይለኝም ። በዛ ላይ ልጁ ትንሽ በራሱ የተሞላ ልብ አድርቅ ነገር ነው ። ይልቅስ ማሚ አንድ ከውጪ የመጣ ሳይኪያትሪስት በቲቪ አይታ ወትውታ ልትገድለኝ ነው ። እሱም ላጭር ጊዜ እዛው ጳውሎስ ነው የሚሠራው መሰለኝ ። እሱን ካላየሁ ብላ ልትሞት ነው ። ያንቺ ሲራክ ጋ ደውዬለት እንግባባለን ሊያያቸው ይችላል ብሎኝ ነበር ባለፈው ሳምንት" አለች ፣ አይኗን ቦዘዝ አድርጋ ባርምሞ እያየቻት ።

"እኔም ኮ ጠርጥሬያለሁ ሚሲ ... በማሚ እያሳበብሽ እንዲህ ነው እንጂ ልጂት ። ዳያስፖራው ይሻላል ብለሽ ነው? ግን አሪፍ አትችኩልም ትዪ የለ ... ሁሉም ነገር ቀስ ቀስ እያሉ ነው ። የምር ቀልጠፍ ነው ... ካልሆነ ደግሞ ይቀራል ... እንኳን ሰው ኩላሊትስ ይቀየር የለ እንዴ?" ስትል ፣ የያዘችውን ትራስ መረመርችባት ። በትራሷ መክታ በተራዋ የሷን ትራስ ስትወርውርባት አፍና ያዘችው ። እሁዱ ሙሉ ቀኑን የባጥ የቆጡን እያወሩ ማሳሸና ሳውና ፣ ዋናና የጀልባ ጉዞ ሲሉ ቀኑ ላይታወቃቸው አለቀ ።

በማግስቱ ሰኞ ከሰዓት በኋላ ላይ ዘግየት ብለው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

መንገዱ እንደ ወትሮው የተጨናነቀ አልነበረም ። የመቅደም አባዜ የያዛቸው ቀሾቃሻ ሚኒባሶችና ሸክም ከብዷቸው እየቃተቱ የሚጎተቱ ከባድ መኪኖች የሚፈጥሩት መላ ያጣ አነዳድ ብቻ አልፎ አልፎ ጭንቅንቅ ይፈጥራል ። አንድ ጊዜ ቀለበት መንገዱ ውስጥ ከገቡ በኋላ በበለጠ በፍጥነት መንዳት ቻሉ ። ጉርዱ ሸላ አካባቢ ሲደርሱ ያለ ወትሮው ጸጥ ብሎ የዋለውን ስልኳን አወጥታ ስታየው ባትሪው አልቆ ጠፍቷል ። የመኪናው የባትሪ ሃይል መሙያ ላይ እየሰካችው ፣

"አይገርምሽም ማታ ቻርጅ ሳላደርገው ባትሪው አልቆ ነው ለካ ። ስልኩ መጥፋቱንም ልብ አላልኩትም ነበር ። እኔኮ ያለወትሮ ዝምታው ገርሞኛል ። ማማ ይሄኔ ነፍሷ ሊወጣ ደርሷል ። አይ አም ሹር እስካሁን መቶ ጊዜ ደውላለች ። "

"ግን ምን አስጨነቀሽ አንቺ? ዝም ብለሽ እኮ ነው ። እንደ እኔ እንደ እኔ ... ቢያንስ ትናንትን ብትገኚላቸው ምንም አልነበረም" ስትላት ፣ ኮስተር ተር አለችና በቃ በሚል አይነት እጇን ከፍ አድርጋ ፣

"አዪ ማርቲ ... እያወቅሽ አታስለፍልፊኝ" አለች ፣ ማወራትም እንዳልፈለገች ። እነ ማርታ ቤት ሲደርሱ አስራ ሁለት ሰአት አካባቢ ነበር ። ግቢ ውስጥ ቀመው እያወሩ የምስጢር ስልክ ደጋግሞ ጮኸ ። የማታውቀው ቁጥር ስለነበር እያመነታች አነሳችውና ፣

"ማነው በናትሽ ዝም ብሎ ደጋግሞ የሚደውልልኝ" ብላ "ሃ...ሎ" ስትል ፣

"እ-ን--ዴ---ት ነሽ የኔ ልእልት ... ደብረዘይት ጥሩ ነበር? በጣም አምሮብሽ ነበር" አለ ጉርንን ያለ የሚጎተትና የምታውቀው ድምጽ ።

በድንጋጤ ስልኩን ከእጇ ላይ የመወርወር ያህል ጣለችውና ፣ "እሱ ነው ፣ እሱ ነው ፣ ወይኔ ማማዬ ፣ ደብረዘይት እንደ ነበርኩ ሁሉ ያውቃል ። ቁጥሬን ደግሞ ከየት አግኝቶት ነው ይባላል?" አለች ፣ የጓደኛዋን ትከሻ ጭምድድ አድርጋ ።

ማርታም ግራ ገብቷት ፣ "ምንድነው እሱ? ማነው? ምን ሆነሻል?" ስትላት ፣

"ማስረሻ ነው ፤ ማስረሻ ነው የደወለው ። ደህና ታግሶለት ጠፍቶ ነበር ። ደግሞ ሊነሳበት ነው መሰለኝ" አለች ፣ መርበትበቷ ሳይቀንስ ።

"ቀይ ተረጋጊ እስኪ ። በመጀመሪያ ፣ እርግጠኛ ነሽ እሱ ነው? ቀይ ውጪ ሄዷል ተብሎ አልነበረም እንዴ? ምን አይነት ጣጣ ነው ባክቹ ። ግን እርግጠኛ ነሽ እሱ ነው?" አለች ፣ ስልኩን ከወደቀበት አንስታ ቁጥሩን እያየች ።

"አዎ ራሱ ነው ማርቲ ። ደብረዘይትም ተከትሎን መጥቶ ነበር ማለት ነው ። በቃ አሁን ሳይመሽ በጊዜ ልሂድ ፤ ማማም ታስባለች" አለች ፣ በመርበትበት ደጅ ደጁን እያየች ።

"ቀይ ብራዘርን ልጥራውና ፣ ለማንኛውም ተከታትለን እንሸኝሽ ። ዩ ነቨር

Brought to You by t.me/bookshelf99

ናው፣ ይሄ እብድ የሆነ ሰውዬ እንዲያው ምን ይሻለዋል? ምን አይነት አበሳ ነው በናታቹ። አይዞሽ ቀንጅዬ" አለች፣ ተንጠራርታ እያቀፈቻት። ወንድሟን ከቤት ለመጥራት ስትደውል፣ ምስጢርም ለእናቷ 'እየመጣሁ ነው፣ መንገድ ላይ ነኝ' ብላ ነገረቻቸው። ማስረሻ ከዩኒቨርስቲ ተማሪነቷ ጀምሮ እየተከታተለ መከራዋን ሲያሳያት የኖረ እወድሻለሁ ባይ እያደባ የሚከታተላት ሰው ነው። እንዲተዋት ያላደረገችውና ያልሞከረችው ነገር ባይኖርም ትቶ ሊተዋት አልቻለም። ላለፉት ዘጠኝ ወራት ጥፍት ብሎ ከርሞ አሁን ደግሞ ድንገት መከሰቱ ነው። ብዙ ጊዜ ሊገድላት ዝቷል።

ማርታ ለወንድሟ ከነምስጢር ቤት እቃ ይዘን እንምጣ ብላው፣ እሱ እየተከተላቸው ወደ የረር ጃክሮስ አመሩ። ሰአቱ ማታ አንድ ተኩል ሊሆን ነው። እቤት ሲደርሱ በመጠኑ መረጋጋት ችላ ነበር። ማርታ የምስጢርን እናት በቁሟ ሰላም ብላ፣ እራት ብዬ ብትባልም ሰው አቁሜያለሁ ብላ ፈጥና ወጣች። ሳሎን ውስጥ ለብቻቸው ተቀምጠው ቲቪ ሲያዩ የነበሩት እናቷ ልጃቸውን ሲያዩ ከሜንቀታቸው ተንፈስ አሉ። ቁጣቸው እንደማይሰራ ስለገባቸው ለማኩረፍ ሞከሩ። ልታዋራቸው በሞከረች ቁጥር ወይ አሜር መልስ ይሰጧታል ወይ ደግሞ ትከሻቸውን እየነቀነቁ አይናቸውን ቴሌቪዥኑ ላይ ሰክተው ዝም አሏት።

"በናትሽ ማሚዬ ተቀጥተሻል አውቃለሁ ... ይገባኛል እኮ... እሺ በቃ ... ሶ--ሪ በጣም... ካሰብኩት በላይ ፕሮግራሜ አቀየኝና በጊዜ መምጣትም አልቻልኩም። ፕ--ሊ--ስ" አለች፣ ግድግዳውን ደገፍ ብላ ጫማዎቿን ከእግሯ አውልቃ ወዲያና ወዲህ እያሸቀነጠረቻቸው። የለበሰችውን ስስ ጃኬት አንዱ ሶፋ ላይ ወረወረችና የናቷን ጉንጭ በግድ ስባ በስሱ ሳመቻቸው። አጠገባቸው እንዘጭ ብላ ተቀመጠችና በረጅሙ ተነፈሰች። ቁጣቸው የማይቀየው እናቷም ስሜታቸው ትንሽ በረድ ሲልላቸው በግርምት አይን የጎሪጥ እያዩዋት

"ምነው ልጄ እንዲያው ሰው ያስባልም አትይም እንዴ? እንግዳው ሁሉ ሚሚስ ሚሚስ ሲል፣ እኔንም እኮ አሳጣሽኝ። ደጅ ደጁን እንዳዩ ነው የሄዱት፣ ያባትሽ ዘመዶችማ በቃ ሳይቀየሙም አይቀር። ቢያንስ ማለቂያው ላይ ብቅ ብለሽ ፊትሽን ብታስመቺ ምናለ። ደግሞ ስልክሽን እንኳ ብትመልሽስ ልጄ? ስልክ መዝጋት ደግሞ ከመቼ ወዲህ ያመጣሽው ጸባይ ነው?" ሲሉ፣ የበለጠ ተጠጋቻቸውና እጇን አንገታቸው ላይ ጠምጥማ ዓይን ዓይናቸውን እያየች።

"ስልኩ ባትሪ ሞቶብኝ ነው እኮ። ማሚዬ ሙች፣ አታምኚኝም? ደግሞ ማሚዬ ያው ታውቂው የለ፤ እዚህ ተሰብስበው እኮ ሰው መቦጨቅ እንጂ ሌላ ምን ሥራ አላቸው ብለሽ ነው። በቃ ድክም እኮ ነው የሚያደርጉኝ። ትዬ ዘሚስ ... መቼ ሄደች? በጣም ነው የናፈቀችኝ" አለች፣ በዛውም የነገሩን አቅጣጫ ለማስቀየር።

"ባሏ ድንገት ታሞባት ሆስፒታል ስለ ገባ መምጣት አልቻለችም። ደውላ ግን ሰላም ብላሻለች። ሻል ካለው ለሚቀጥለው እሁድ እመጣለሁ ብላለች።"

Brought to You by t.me/bookshelf99

ከሚች ባለቤታቸው ዘመዶች ወይዘሮ ዘምዘም ብቸኛ የቅርብ ጓደኛቸውና የረጅም ጊዜ ምስጢረኛቸው ናት ። ሚስጥርም ከአባቷ ዘመዶች የምትቀርበው እርሷን ብቻ ነው ።

"ውይ ምን ሆነ?" አለች ፣ ደንገጥ ብላ ።

"ያንጀት መታጠፍ ነው መሰለኝ ያለችኝ ። "

"የኔ ናት አሁን እሱ ለራሱ ምን አንጀት አለውና ነው በናትሽ ። እስኪ ነገ ደውዬላት እሄዳለሁ" ብላ ፣ አጠገባቸው ተመቻችታ ተቀመጠች ።

የምስጢር አባት ገና በህይወት እያሉ ነበር ያላቸውን ንብረት ሁሉ በስሟ አዛውረው ሙሉ ወራሽ ያደረጓት ። ይህም ሆኖ ከአባቷ ሞት በኋላ እናቷንና እሷን ከንብረታቸው ለማፈናቀልና ለመቀራመት ቤተሰቡ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም ። በተጨማሪም አባቷ በጠና በታመሙ ጊዜ ወይዘሮ ዘምዘም ብቻ ነበረች ከጎናቸው የቀመችው ። ድንገት ብድግ አለችና ከቴሌቭዥኑ አንጻር ከፍ ብሎ የተቀመጠውን ትልቅ ያባቷን ፎቶግራፍ አንስታ በፊቱ ደፍታ ከታችኛው መደርደሪያ ላይ ስታስቀምጠው

"እንዴ! ምነው ልጄ ፣ ደግሞ እሱ ምን አደረገሽ? ለዛሬ እንኳን ይሁን እስኪ" አሉ እያመነቱ ።

ወደ እርሳቸው ዞር ብላ ቀጣ ባለ ድምጽ ፣ "ይበቃዋል ... ይበቃዋል ። በህይወት እያለ ያፈጠጠብን ይበቃዋል ። ቤቱ ህያዋን የሚኖሩበት እንጂ ሙታን በመንፈሳቸው የሚገዙበት አይደለም ። እንዲያውም ነገ የሆነ ቦታ ካላስገባሽው ወደ ጓሮ ሊጣልም ይችላል ። ሁሉም ያው ናቸው ። ያሉትም ከሞቱት አይሻሉም ። የራሳቸውን ሙት ህይወት ለማረሳሳት ፣ ሌላ ሚች ለማኖር ይንገዳገዳሉ" አለች ፣ ስሜቷ እየጋለ ። አነጋገሯ ደንገጥ ቢያደርጋቸውም የውስጥ ስሜቷን ስለሚረዱ ፣ ደግሞም በዚያ ሰዓት ከርሷ ጋር ለመሟገት ምንም ፍላጎት ስላልነበራቸው ወሬያቸውን ወደ ሌላ ሃሳብ ቀየሩት ።

"እስኪ ቴሌቪዥኑን ክፈቺው ሚሚዬ ሰአቱም ደርሷል መሰል እኮ ። "

"የምኑ ነው ሠዓት ነው የደረሰው?" አለች ፣ ሠዓቷን እያየች ። ትንሽ እንደ መቁነጥነጥ እያደርጋቸው

"ረሳሽው እንዴ ልጄ? ያ ዶክተሩ ፣ ማን ነበር? ዶክተር ሌላሠው ነዋ ። ጳውሎስ ነው የሚሰራው ብለዋል ብዬሽ ነበር ። ጓደኞችሽን ጠይቂሽ ቀጠሮ ልታስይዝልኝ አልነበር እንዴ? ያንቺ ነገር ፣ ይሄኔ ረስተሽዋል እኮ ። የቴሌቪዥኑ ኢንተርቪው የመጨረሻው ክፍል ዛሬ ነው ። አስራ ምስት ደቂቃ ነው የቀረው ሊጀምር"

"አይ አልረሳሁትም ማሚ ። እንዲያውም እዛ የሚሰራ አንድ የማውቀው ዶክተር አለ ። ለሱ በቀደም ደውዬለት ነግሬው ነበር ። ቀይ እንዲያውም አሁን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ልጠይቀው እስኪ" አለችና፣ ትንሽ ተንጠራርታ፣ "ኡ...ፍ... ፍ ... ድክም ብሎኛል። እስኪ በዛውም ልብሴንም ቀያይሬ መጣሁ። ውሃም ጥምት ነው ያለኝ፣ ሄደች።

"እንዳያመልጥሽ ቶሎ ነይ ታዲያ ..." ሲሉ፣ ዞር ብላ በፈገግታ አየት አድርጋቸው

"እደርሳለሁ ማሚዬ። ካልደከማቸው ልጆቹ ቡና ቢያፈሉልን እንዴት ጥሩ ነበር።" መኝታ ቤቷ እንደ ገባች ከቦርሳዋ ውስጥ ስልኳን አወጣችና ወለሉ ላይ ጣል አደረገችው። አልጋዋ ላይ የመወርወር ያህል ተዘረረችና በጀርባዋ ተንጋላ ጣራ ጣራውን እያየች ጥቂት ቆየች። ከዚያም ከቁጥሮቹ መሃል ዶክተር ሲራክ የሚለውን መርጣ ደወለች።

አንዴ እንደ ጮኸ አነሳው። "ሃሎ ... ሃሎ ... ሚ-ስ-ጥ-ር? ታዲያስ ... ሰላም ነው?" አለ በሽቁጥቁጥ አነጋገር።

"ሄ--ይ ዶክተ-ሩ እን-ት ነህ" አለች፣ ቅላጼው ሞልቀቅ ባለና ሙዚቃዊ ለዛ በተሞላ ድምጽ።

"አለን ደህና፣ ያው ሥራ ምናምን ትንሽ ይበዛል። ደውዬልሽ እኮ ስልክሽ እምቢ አለኝ። አሁን እንደገና ልሞክር ስል ነው የደወልሽው። የናትሽን ጉዳይ፣ ዶክተር ሌላሠው ነገ ጠዋት ይምጡ ብሏል። ብታይ በጣም የተመቸው ቀሽት ሰው ነው። አለ አይደል ... የገባው ነገር ... አሪፍ ሳይኪያትሪስት ነው" አለ፣ ፈጠን ባለ ድምጽ። ግዳዩን መጣሉ ነጥብ እንደሚያሰጠው ተስፋ አድርጓል።

"ሪሊይ? አንተ ይህንን ያህል ካደነቅኸው፣ እውነትም አሪፍ መሆን አለበት። እናቴ ደግሞ እንዴት እንደምትመርቅህ ልነግርህ አልችልም። ታዲያ ስንት ሰአት ብንደርስ ጥሩ ነው?" አለች። ሲራክ እንኳን እንዲህ ለማድነቅ ቀርቶ ለብዙ ሰዎች ያለው ንቀት ሰማይ የነካ እንደሆነ ስለምታውቅ ገርሟታል።

"በቃ ሦስት ሰአት አካባቢ ብትደርሱ፣ ከጠዋት ስብሰባ እንደወጣ ሰው ሳይበዛ መጀመሪያ ሊያያቸው ይችላል። ከቻላችሁ ለምን እዛ ... በጎን በር በኩል ያለችው ካፌ አንገናኝም። እኔም ከቀደምኳችሁ እዛው እጠብቃችኋለሁ"

"በጣም ... አሪፍ ነው። እዛው አይሃለኋ እንግዲያው። ታንክ ዩ ሶ ማች እሺ ሪ...ሊ....ይ ..." አለች፣ ደስ ብሏት።

"ኧረ ምንም አይደል፣ ሌላስ ነገር ቢሆን"

"እኔ የምልህ አንተ ግን በዚህ ወር ጳውሎስ አይደለሁም ያልከኝ መስሎኝ ባለፈው። ለኛ ብለህ ነው እዛ ድረስ የምትመጣው?" አለች፣ አማኑኤል ነኝ ያላት ትዝ ብሏት።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አ-ዎ-ን አማኑኤል ነኝ። ነገ ግን ብዙም የሚያስቸኩል ነገር ስለሌለኝ አንዳፍታ ከርሱ ጋር አገናኝቼያችሁ መሄድ እችላለሁ" አለ፣ ነገሩን ቀለል እያደረገ።

"ኦ-ህ ታንክ ዩ ኤጌይን ... ራ-ሊ-ይ ... ዛት ኢዝ ሶ ናይስ ኦፍ ዩ" አለች።

ወሬዋ ብዙ ጊዜ እንግሊዝኛ ይበዛዋል። ሪሊይ የምትልበት የራሷ ሙዚቃዊ ቃናም አላት።

"እሪ ምንም አይደለም ... ኢት ኢዝ ማይ ፕሌዠር ..." ብሎ፣ እሱም ንግግሩ ውስጥ ለማርከሻ ያህል እንግሊዝኛ ጣል አደረገበት። ሌላ ወሬ ያለቀባቸው ይመስል ጥቂት ጸጥ አሉ።

"በቃ ነገ አገኝሃለሁኝ። አሁን ማሚም እየጠበቀችኝ ስለሆነ ልሂድና ልንገራት። እንዴት ደስ እንደሚላት ... ቻዎ እሺ" ብላው ተሰናበቱ። ስልኩን ከዘጋች በኋላ እንደ ተጋደመች ውል የሌለው ሃሳብ ስትፈታ ስትቋጥር ትንሽ ቀየች።

እንደ ምንም አቅሟን ሰብስባ ከተጋደመችበት ብድግ አለችና ከቁም ሳጥኑ ውስጥ የምትቀይረውን ፒጃማና ፎጣ አወጣች። ልብሶቿን አወላልቃ አልጋው ላይ እንደ ነገሩ ወርውራ ሻወር ውስጥ ዘላ ገባች። ሰውነቷን እያደራረቀችና እየተቀባባች ከመስታዋቱ ፊት እንደቆመች ቀን ስትሰማ የዋለችውን አዲስ ሙዚቃ ለራሷ ማንጎራጎር ጀመረች።

የቀዳዋ መልክ ጥይምና ወደ ቅላት ያዘነብላል። ሰውነቷ ሞላ ያለ ቢሆንም ደስ የሚል የሴትነት ቅርጿ በቀላሉ ዓይን ይገዛል። በመካከለኛ ቁመቷ ላይ ሁሌም ከፍ ያለ ጫማ ስለምታደርግ ከሆነችው በላይ ረጅም ትመስላለች። አይኖቿ ትልልቅ የሚባሉ ባይሆኑም በስሜት የተሞሉና ጥቅጥቅ ባለ ሽፋል የተከበቡ ናቸው። ከማየት ተግባራቸው በላይ እንደሚያበሩ ባለፈርጥ ጌቦች ታይተው አይጠገቡም። በተለይ ስታቦዛቸውና ስትስቅባቸው የበለጠ ያምራሉ። ጸጉሯ ሁሌም አጭር ነው። ከብዛቱ ጋር ፍሪዝ ስታደርገው ፊቷን በጥቁር ጫካ የተከበበ ውብ መስክ ያስመስለዋል። ፒጃማዋን ለባብሳ እንደ ልማዷ እየተንደረደረችና ደረጃውን እያንደዛደዘች ወደ ላሎን ስትደርስ ፕሮግራሙ ተጀምሮ ነበር።

"ብዙ አመለጠኝ እንዴ ማሚዬ?" አለች፣ አጠገባችው ተቀምጣ ጋቢያቸውን ለመጋራት እየሞከረች።

"አይ ብዙም አይደል፣ ስጠራሽ እኮ ሻወር ውስጥ ነበርሽ መሰል አልሰማሽኝም። ደወልሽ እንዴ ጓደኞችሽ ጋ?" አሉ፣ መጓጓታቸው በሚያስታውቅ ድምጽ ጋቢውን የበለጠ እንድትጋራ እያስተካከሉላት።

"አዎን ለነገ ጠዋት ቀጠሮ አስይዘውልሻል። መጀመሪያ እንዲያይሽ ሶስት ሰአት መድረስ ይኖርብናል" አለች፣ ሙሉ ለሙሉ ሶፋው ላይ እግሮቿን አውጥታ በጋቢው ተሸፋፍና እየተቀመጠች። እውነት እንዳልመሰላቸው ሁሉ ድንግጥ ብለው

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ነገ? ... ከዶክተር ሌላሠው ከሱ ጋር?" አሉ፣ ዓይናቸውን ሚስጢር ላይ እንደ ተከሉ ወደ ቴሌቪዥኑ ጣታቸውን እየጠቀሙ። የናቷ አባባል የገረማት በሚመስል እይታ አፏን ጠመም አድርጋ

"አዎና፣ ማሚ ደግሞ ዝም ብለሽ ነው እኮ የምታካብጂው። እሱ የሆነ እንደሆነ ምንድነው? ምን የተለየ ነገር አለው ብለሽ ነው" አለች፣ ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ። ምናልባት ብዙ ነገር ጠብቀው ተስፋ እንዳይቀርጡም ሰግታለች።

"አይ ልጄ ... አንቺ የማታውቂው ስንት ጉድ ... ስንት ህመም አለኝ መሰለሽ። ይሄን ዶክተር ፈጣሪ ለኔ ብሎ፣ መድሐኒያለም የነገሩትን የማይረሳ የጠየቁትን የማይነሳ በጥበቡ የላከልኝ መፍትሄ ነው። በጣም ነው የማመሰግንሽ" ብለው፣ ራሷን እያሻሹ ትክዝ ሲሉ፣

"እንዴ ማሚ ደግሞ ምንድነው እንደዚህ መሆን። ደግሞ እኔን የምታመሰግኚው ምን አድርጌልሽ ነው? ምንድነው እኔ ማላውቀው ችግር አለ እንዴ?"

"አይ ተዪው፣ እንዲየው ዝም ብዬ ነው። እስኪ ድምጹን ጨመር አድርጊው። ለዛሬ ያለውን ውይይት ሊጀምሩ ነው መሰል" አሉና ተመቻችተው ተቀመጡ። ጋዜጠኛዋ አስቀድማ የመግቢያ ማስተዋወቂያዋንና ስላለፈው ሳምንት ንግግራቸው አጠቃላይ የክለሳ መግለጫ ሰጠች። አስከትላ በጭንቀትና በፍርሃት ዙሪያ ላቀረበችለት የመጀመሪያ አጠቃላይ ጥያቄ መልስ በመስጠት ላይ ነበር

"ባጠቃላይ ጭንቀት የሚለው ያማርኛ ቃል ለብዙ ነገር ስለምንጠቀምበት የሚወክለውን ትክክለኛ የስሜት ስቃይና ህመም ለመለየት አዳጋች ነው። ለድብርትም፣ ለአእምሮ መታወክም፣ እንዲሁም ለሌሎች ድብስብስ ስሜቶች ሁሉ ጭንቀት የሚለውን ቃል ስለምንጠቀምበት እሱን ትንሽ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ዛሬ ከምናወራው ሃሳብ አንጻር ጭንቀት የምንለው ውጥረት ያየለበት በጊዜው በእውኑ አለም ከተፈጠረ ክስተት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና የሌለው ወይም ከእውነታው ጋር ያልተመጣጠነና የተጋነነ የፍርሃት ስሜትን ነው።

"ፍርሃት በምንልበት ጊዜ ግን በየዕለቱ ኑሮአችን ላሉ በእውኑ አለም አስፈሪ ለሆኑ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች የምናሳየው ስሜት ስለሆነ ብዙ አሻሚ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ብቻሽን ሆነሽ አውሬ ቢመጣብሽ፣ ፎቅ ላይ ሆነሽ እሳት ቢነሳ፣ የታጠቁ ሌቦች ባላሰብሽው ሰአት ድንገት ቢያግቱሽ ... ይሄ የሚፈጥረው የፍርሃት ስሜት የጤና እንጂ የበሽታ ሊባል አይችልም።

"ነገር ግን አንድ ሰው ባለፈ ጊዜ ውስጥ ያጋጠመው አሰቃቂና አስፈሪ ሁኔታ ልክ ዛሬ እንደሆነ በፍርሃት ጠፍሮ ሲይዘው ... ወይም ... ገና ለገና ወደፊት ይደርስብኛል አልያም ይሆናል ብሎ ውስጡ በሚፈጠረው ስጋት ከልክ ባለፈ ፍርሃት ሕይወቱ ቢመሰቃቀል ህመም ሊሆን ይችላል።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"እ ም...ም ... ወይም ደግሞ ለምሳሌ እንደ ሽረሪትና የመሳሰሉ ሌሎች በአብዛኛው ሰዎች ከምንም የማይቀጥሯቸውንና አደጋ የማይፈጥሩ ነገሮችን፣ ማየቱም ሆነ በአካባቢው መኖራቸውን በማሰብ ብቻ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ፍርሃት ሲርበደበድ ... 'አንዛይቲ' ብለን በምንጠራቸው የተለያዩ ከፍተኛ የጭንቀትና የመረበሽ ስሜት ያዘሉ የአእምሮ ህመም አይነቶች እየተሰቃየ ሊሆን ይችላል።

"ሁሉንም በደምሳሳው የጭንቀት ህመም ወይም 'አንዛይቲ' ብንላቸውም የተለያዩ ህመሞችን በስሩ አቅፎ የያዘ ጥቅል የህመም አይነት ነው" ብሎ መለሰ።

ምስጢር አፏን ጠመም አድርጋ፣ "ኧረ ... ኧረ ... ሰውዬው ካሜሪካ ነው ከጎንደር የመጣው? አማርኛው እንዴት አሪፍ ነው ባክሽ። ደግሞ ዘናጭ ቢጤ ነገር ይመስላል። እኔ እኮ በጣም ትልቅ ሰው መስሎኝ ነበር" አለች።

"እኔም ባለፈው ሳምንት ካየሁት በኋላ ቀልቤ በጣም ነው የወደደው" አሉና የሚቀጥለውን ጥያቄ ለመስማት ዝም አሉ።

ጋዜጠኛዋ ጥያቄዋን ቀጠለች። "እሺ ዶክተር ነገሩን እንዳልከው ለጊዜው የጭንቀት ወይም የፍርሃት ህመም እንበለው። አይነቱም መንስኤውም ብዙ ነው ብለኸናል። እኛ አገር ደግሞ እነዚህ ህመሞች ገና ህመም እንደሆኑ እንኳ ግልጽ የሆነ ስም ተሰጥቷቸው እውቅናንም ያገኙ አይመስሉም። ለምሳሌ ብዙ ሰው ቅድም እንዳልከው ሽረሪት፣ አይጥ፣ ድልድይ፣ ጨለማ ምን ልበልህ ብዙ ነገር ይፈራል... ለምሳሌ እኔ አንድ ጓደኛ አለኝ ፍየል በጣም ነው የሚፈራው ... የፍየል ፎቶ እንኳ ሲያይ ይቀፈዋል። ይሄንንስ የአእምሮ ህመም ነው ልንል እንችላለን ማለት ነው? መፍትሔስ አለው?" ስትለው

"አዎን ህመም ሊሆን ይችላል። አንድ ነገር የአእምሮ ህመም ሊባል የሚችለው፣ የተፈጠረው የስሜትና የአስተሳሰብ ስቃይ ከፍተኛ ሆኖ የተለመደውን ዕለታዊ የግንኙነት፣ የስራና ማህበራዊ ህይወትን ሲያዛባ ብቻ ነው። ስለዚህ እነዚህ ጥቃቅን የሚመስሉ ፍርሃቶችም የአንድን ሰው ህይወት በመቆጣጠር ከባድ በሽታ ሊሆኑ ይችላሉ።

"በጣም የሚገርምሽ ካሉት የጭንቀታዊ ፍርሃት ህመሞች (አንዛይቲ) ውስጥ ብዙ ሰዎችን በማሰቃየት ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የዚህ ዓይነቱ ችግር ነው። በህክምናው 'ፎቢያ' እንለዋለን። በዋናነት በተለያዩ የምክር ዘዴዎች፣ በተወሰነ መጠን ደግሞ በመድሃኒት የህክምና መፍትሄ ሊኖረው ይችላል። በርግጥ አሁን ካለን ሰአትና ከፕሮግራሙ ይዘት አንጻር ሁሉንም ለመዘርዘር ያዳግታል" ሲል፣ ጋዜጠኛዋ ቀበል አድርጋ፣

"ጥሩ ዶክተር ... ያው እንዳልከው ከጊዜም አንጻር ዝርዝር ውስጥ ለመግባት አስቸጋሪ ነው በርግጥ። ግን በተለይ ዛሬ ትንሽ ገለጥለጥ አድርገን እንድንወያይ የምፈልገው የጭንቀት-ፍርሃት ህመም ዓይነት አለ። ምናልባትም ባገራችን በጣም

Brought to You by t.me/bookshelf99

በከፍተኛ ደረጃ ብዙ ሰው የሚሰቃይበት ጉዳይ ሊሆን ቢችልም ገና ህመምነቱ እንኳ በቅጥ መታውቁንም እጠራጠራለሁ ። በናንተ የህክምና ቋንቋ 'ፖስት ትራውማቲክ ስትረስ ዲስኦርደር' የሚባለውን ማለቴ ነው ። በአማርኛ ለመተርጎም ያስቸግራል ... ምን እንበለው?" አለችና የያዘችውን ወረቀት ከፊት ለፊቷ ያለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች ።

"እ... ም ...ም ያው እንዳልሽው በቀጥታ ወደ አማርኛ መተርጎሙ ከባድ ነው ። ሃሳቡ ግን ሰው ከደረሰበት ከባድ የሆነ አሰቃቂ አደጋ ወይም ክስተት በመከተል የሚፈጠር በሞንቀት የተሞላ የፍርሃት ህመም ነው ። ይሄ አሰቃቂ ክስተት በህመምተኛው ላይ የደረሰ ወይም ህመምተኛው በቀጥታ ባይኑ ያየውና የተሳተፈበት ከፍተኛ አደጋ ወይም ጉዳት ሊሆን ይችላል ። ወይም ደግሞ የቅርብሽ የሆነ ሰው ያለፈበት አስቃቂ ነገርም ሊሆን ይችላል ።

"ለምሳሌ አንዲት ሴት ተገዳ ብትደፈር ወይም ሌላ ሴት ስትደፈር ብታይ ... እም ...ም ወይም በቦር ሜዳ ላይ በሚደርሱ አሰቃቂ ግድያዎች ላይ የተሳተፉ ወይም የቅርብ አጋሮቻቸው በሚዘገንን ሁኔታ ሲገደሉና ስቃይ ሲደርስባቸው ማየት ሊሆን ይችላል ። ሌላው ሕፃናትና አዳጊዎች ላይ የሚደርስ የአካል ፣ የወሲብና የስሜት ጥቃቶች በብዛት የሚታዩ መንስኤዎች ናቸው ።

"እነዚህ ሁሉ እንግዲህ ወዲያው ከሚፈጥሩት ጫናና ስቃይ በተጨማሪ በአእምሯችን የትዝታ ማህደር ውስጥ ለመፋቅና ፈጽሞ ለማጥፋት በማይቻል ሁኔታ ይመዘገባሉ ። ከጊዜ በኋላ በተለያየ ምክንያት አእምሮሽ እነዚህን ያለፉ ክስተቶች ለተወሰነ ጊዜ ቀልፎ ያሸገበት ካዝና ላልቶ ሲከፈት ትዝታዎቹ እየሾለኩ ይወጡና እንደ አዲስ ክስተት መሆን ይጀምራሉ ። ሞንቅላትሽ ልክ እንደ ካሴት እየደጋገመ ሲያጫውታቸው የሚፈጠረው ስቃይ አንዳንድ ጊዜ ነገሩ በተፈጸመበት ጊዜ ከሆነው የከፋ ሊሆን ይችላል ። በኔ ግምት በሀገራችንም በጣም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕፃናትና አዋቂ ሰዎች በዚህ ስቃይ ውስጥ ማንም ሳያውቅላቸው የሚኖሩ ይመስለኛል" ብሎ ፊቱ ካለው ውሃ ጎንጨት አለ ። ምስጢርና እናቷ ጸጥ ብለው ማዳመጥ ተያይዘዋል ። ከፊታቸው የቀረበውን ራትም ልብ ያሉት አይመስልም ።

"ወደ ተጨማሪ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ዶክተር ለምሳሌ የዚህ አይነት ችግር ያለበት ሰው ምን አይነት ምልክቶች ሊታዩበት እንደሚችሉ ብታብራራልን" ብላ ፣ የተቀመጠችበት ሶፋ ላይ ለመመቻቸት ሞከረች ጋዜጠኛዋ ።

"እንግዲህ ያው ከሰው ሰው ቢለያይም አጠቃላይ የሆኑ ምልክቶች አሉ ። በተለይ ሕፃናት ላይ ምልክቶቹ ለየት ሊሉ ይችላሉ ። በወንድና በሴት መካከልም መጠነኛ ልዩነት ሊኖር ይችላል ። እንደ ጉዳቱ ልክ ፣ እንደ የሰዉ የሰብእና አወቃቀርና ነገሮችን የመቋቋም ችሎታ ምልክቱ መለያየቱ አይቀርም ። በአጠቃላይ ግን ሁል ጊዜ በአደጋ ቀጠና ውስጥ እንደሚኖር ሰው በስጋት መሞላት ፣ ከፍ ያለ ድምጽና ጩኸት ሲሰሙ መደንበርና ድንጥጥ መሆን ፣ ሌሊት በእንቅልፍ ቅዠትና ቀንም

Brought to You by t.me/bookshelf99

በንቃት ሰአት ላይ የደረሰባቸውን ወይም የችግሩ መንስኤ የሆነውን ሰቀቃ ደጋግሞ ደጋግሞ በዓይነ ህሊና ማየትና ልክ አሁን እንደሆነ ያህል መሰቃየት ፣ በዚህም የተነሳ በቀላሉ ብስጩና ሆደ ቡቡ መሆንንም ያጠቃልላል ።

"በተጨማሪም ሌሎችን ማመንና ዘና ብሎ መኖር አለመቻል ፣ አንዳንዴም በተለያዩ ሱሶች በመጠመድ ስቃይን የመሸፈን ዝንባሌ ይታያል ። የደረሰውን ሰቀቃ ሊያስታውሱ ከሚችሉ ሰዎችና ሁኔታዎች መሸሽና አንዳንዴም ከፍተኛ የሆነ የስሜት መዋዠቅና ብሎም ከባድ ድባቴ ውስጥ መግባትም በብዛት ይታያል ። ብቸኝነትና ከሰው አለመግባባት ፣ እንቅልፍ ማጣት ፣ ጸጸትና በማይገባ ደረጃ ራስን መውቀስም አለ ። ግን እንዳልኩሽ ነገሩ ከሰው ሰው ይለያያል ፤ ደግሞም ሁሉም ምልክት ሁሉም ሰው ላይ ላይታይ ይችላል" ብሎ ፣ ራሱን እያነቃነቀ እጁን አጣምሮ ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ ተቀመጠና ዝም አለ ።

"ጥሩ ... በጣም ግልጽ ነው ዶክተር ። ግን ቅድም እንዳልከው ችግሩ እዚህ አገራችን ውስጥም ትንሽ የሚባል አይመስለኝም ። በሃገራችን ላለው ችግር እንደ መንስኤ ብለን የምንዘረዝራቸው ዋነኛ ነግሮች ይኖራሉ? ይህን ያህል ችግሩ ብዙ ከሆነስ ለምንድነው ችግሩ ያደባባይ ሚስጥር ሆኖ እያለ ሰው ሁሉ በየቤቱ የሚሰቃየው ትላለህ?" አለችና ማስታወሻዋ ላይ የሆነ ነገር ጫር ጫር አድርጋ ቀና አለች ።

"መንስኤው ብዙ ነው ። ለምሳሌ ከአብዮቱ በኋላ በተቀሰቀሰው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካና የርእዮተ አለም ግጭት ቀይና ነጭ ሽብር ውስጥ ብዙ አሰቃቂ ግድያ ባደባባይ ተፈጽሟል ። በየእስር ቤቱ የተፈጸሙት ግርፋትና ሊነገሩ የማይችሉ ስቃዮችና የሰብአዊ ክብር መደፈር ሰቀቃ ሁሉ ባብዛኛው ሳይታከም በየሰዉ ልቦና ታፍኖና በየቤቱ ታሽጎ ቀርቷል ። ሕፃናት በጠራራ ጸሃይ የወደቁ ሬሳዎችንና ሊሞቱ የሚያጣጥሩ ወጣቶችን አይተዋል ። እናቶች የልጆቻቸውን ሬሳ በገንዘብ ገዝተዋል ።

"ባለፉት አርባ አመታት ብቻ የእርስ በርስና ከጎረቤት አገሮች ጋር የተደረጉ ጦርነቶች የፈጠሩት ጥፋት ፣ የህይወትና የአካል ጉዳት ሁሉ ምንም ቃል ሊገልጸው አይችልም ። ይህ ደግሞ ምንም ዓይነት ህክምና ያላገኘ የስሜት ጠባሳ ብቻ ሳይሆን ያላጠገጉት ቁስሎች ዛሬም በየቤቱና በሰዎች አእምሮ ውስጥ የማይታመን ስቃይን እያጫሩ እንዲኖሩ አድርጓል ። በድርቅና በሌሎች ተፈጥሮአዊ አደጋ ስበብ በደረሰባቸው መፈናቀልና መከራም በዚህ ሀመም የሚሰቃዩ ብዙ ሰዎች አሉ ።

"ሌላው ብዙ ጊዜ አትኩሮት የማይሰጠው ... ለምሳሌ በቤት ሰራተኞች ላይ በየቀኑ የሚደርሰው የወሲብና የአካል ጥቃት ነው ። በህጻናት ላይ በቤተሰብና በጎረቤት ባሉ አዋቂዎች የሚደረገው ወሲባዊም ሆነ አካላዊ ጥቃትና መደፈር ያልተነገረ ሥነልቦናዊ እዳ ነው ። ሌላው ቀርቶ ተጋብተው በሚኖሩ ሴቶች ላይ በባሎቻቸው የሚደርሱ አካላዊ ጥቃቶችና አስገድዶ መድፈሮች ሁሉ ቀላል

Brought to You by t.me/bookshelf99

እንዳይመስሉሽ ። ባህላችን ብዙ ነገሮችን ከድኖ እንዳላየ የሚያልፍና ድብቅ ስለሆነ ይሄ ነው የማይባል ቁስል በየቤቱ እያመረቀዘ ይኖራል ።"

የቡና እቃውን አቀራርባ ወጣ ገባ ስትል የነበረችው ልጅ ስትፈራ ስትቸር "ትዬ ቡናው ይፈላ ወይስ እስክትጨርሱ ..." አለች ፣ እጇን አፏ ላይ አድርጋ ።

"አይ ትንሽ ይቀየን ... አንዴ ይህቺን እንጨርስና ይደርሳል..." አሏት ፣ አይናቸውና ግማሽ ልባቸው ቲቪው ላይ እንደ ተሰካ ። የዶክተሩ ቃለ ምልልስ እንደቀጠለ ነበር ።

"እና ... አንዳንዴ የድብቅነት ባህላችንን ከምን ጋር ይመሳሰልብኛል መሰለሽ? ... አስቢው ከደጅ የሚታዩትን በረንዳችንንና አጥራችንን እንዴት እንደምናሳምር ። ደግሞ የበለጠ የሚጠቅሙንንና የምንጠቀምባቸውን ኩሽናዎቻችንና የሽንት ቤቶቻችን ደግሞ በየቤቱ ፣ በየመስሪያ ቤቱና ሆቴሉ ምን እንደሚመስሉ እስኪ አስቢያቸው ። አንዳንዴ እንኳን ለማየትና ለመጠቀም ቀርቶ ለማሰብም ይዘገንናሉ ። ይሄ ደግሞ ለብዙዎቻችን እንግዳ ነገር አይመስለኝም ። ልክ እንደዚሁ ወደ ሰዉ የውስጥ ሕይወትና ያለፈ ታሪክ ስትገቢም 'ገመና መደበቅ' በሚለው የአስተሳሰብ ቦስ ብዙ ሰቀቃና የስሜት ስቃይ ትዝታዎች ምስጢር ሆነውና ተቀብረው እንደታፈኑ ይኖራሉ ። ውጪውን ስታዪው ብዙ ሰው ሳቂታና ደስተኛ ቢመስልም" አለ ። በተመለጦ ስትሰማው የነበረችው ጋዜጠኛ ሌሎች ጥያቄዎችንም አከታትላ ጠየቀችው ። ምስጢርና እናቷም በጸጥታ ሲያዳምጡ ቆዩ ።

"ማማዬ የሚለው ሁሉ ኮ ልክ ነው ። ግን ደግሞ በቃ ምን ያደርጋል ችግሩ ተራራ መፍትሄው ግን ጠጠር ነው ። ማነው ይህን ሁሉ ጉድ ከየቤቱ ለቅሞ እያወጣ የሚያከመው ። ሆስፒታልስ ልሂድ ቢባል የት ነው የሚኬደው? አይ ቲንክ እሱን ማየትሽ ጥሩ ይመስለኛል" ብላ ፣ ተንጠራርታ ተነሳች ። ማስታወቂያዎች እስኪታዩ ልጆቹን ጠርታ ወጦቹንና ቡናውን እንደገና አሙቀው እንዲያመጡት ነገረቻቸው ። ከማስታወቂያው በማስከተልም ፣ ስለ ችግሮቹ መፍትሔዎችና ያሉትን የህክምና አማራጮች በተመለከተ ሃሳብ ሠጥቶ ፣ በሌላ ጊዜ ተመልሶ በተያያዥ ችግሮች ላይ ውይይቱን ለመቀጠል ቃል ገብቶላት ፕሮግራሙ ተጠናቀቀ ።

እራት እየበሉም በጉዳዩ ሲጨዋወቱ ቆዩ ። ቡናው አልቆ ሲነሳሳ ስልክ ሲመጣባት ጉንጯቸውን ሳም አድርጋቸው ወደ መኝታ ቤቷ ሄደች ። እናቷ ግን በተቀመጡበት በአሳብ ሟልጥ ብለው ሄዱ ። አንዴ በራሳቸው የህይወት ምህዋር ሲዞሩ ፣ ደግሞ ስለ ምስጢር ሲጨነቁና ሲብሰለሰሉ ፣ ከዛም ስለሚች ባላቸው በትዝታ ሰረገላ ተሞነው ሲማስኑ ቆዩ ። ድካሙና እንቅልፉ ሲጫጫናቸው ፣ እንደ ምንም ከሶፋው ላይ ተነሱና ለብቻው የሚጮኸውን ቲቪ አጥፍተው ወደ መኝታቸው ሄደው ጋደም አሉ ። አብዛኛው ሌሊት እንቅልፍ አልባና ቅዠት የሞላበት ሆኖ ሲባንኑና ሲያሸልቡ ነበር የተገባደደው ። እንዳይቀር ያህል ወደ ማነጋጊያው ላይ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

7

ወይዘሮ ኤደን ጠዋት ላይ ምስጢር ስትቀሰቅሳቸው፣ ሰውነታቸው ከብት ሲሄድበት እንደዋለ ማሳ ተደቅድቆ፣ ድቅቅ ብለው ካልጋቸው በግድ ወጡ። ትንሽ ቀለል ቢለኝ ብለው ቁርስ ቢጤ ከአንድ ስኒ ጥቁር ቡና ጋር አፋቸው አደረጉ። እሷ ግን ለምዶባት ቀኑ ሞቅ ካላለ ምንም ነገር ወዳፏ አይገባላትም። ብቻ ቀዝቀዛ ውሃ ውስጥ ሎሚ ጨምቃ በባዶ ሆዷ መጠጣት የሁል ጊዜም ልማዷ ነው። ከሰፈራቸው እስከ ጳውሎስ ሆስፒታል ድረስ የጧት መንገዱ ብዙ ውጣ ውረድ ስላለው፣ ላለማርፈድ በጊዜ ወጡ። መንገዱ ክፍት ስለ ነበረ ሁለት ሰአት ተኩል ላይ ደረሱ። መኪናቸውን ሲያቆሙ ካፈው አካባቢ ሲጠብቃቸው የነበረው ሲራክ ምስጢርን ከሩቅ አይቶ ወደ እነርሱ መጣ።

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ "በጣም ነው የምናመሰግነው ... በጠዋት አደከምንህ አይደል?"

"ምን መንገዱ እኮ ደህና ነው ስትዪው አቁሞ ያውልሻል፣ ይዘጋጋል ብለሽ ስትፈሪ ደግሞ ባዶ ይሆናል ..." አለ።

ፈገግ እንዳለች ወደ እናቷ ዞር ብላ፣ "ማሚዬ ዶክተር ሲራክ ይባላል። ከዶክተር ሌላው ጋር ቀጠሮ ያስያዘልሽ እሱ ነው። የአእምሮ ህክምና ስፔሻሊስት ለመሆን እያጠና ነው። ዘንድሮ ነው አይደል የምትጨርሰው ዶክተር?"

"ልክ ነው፤ እግዜር ካለ ዘንድሮ ያልቃል" አለ፣ ካንገቱ ሰበር ብሎ እናቷን በሁለት እጁ እየጨበጠ።

"በጣም ነው የማመሰግነው ዶክተር። መቼም ጥሩ ሰው አይጥፋ። አንተም እዚሁ ሆስፒታል ነው የምትሠራው እንዴ ታዲያ?" አሉ፣ አይናቸውን ከርሱ ላይ ሳይነቅሉ እንደ ማጥናት ዓይነት እየቃኙት።

"አይ እሱ በዚህ ወር አማኑኤል ነው ያለው። ላንቺ ብሎ ነው ከዶክተር

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሌላሠው ጋር ሊያገናኝ እዚህ ድረስ መጥቶ የጠበቀን" አለች ፣ ፈጠን ብላ ፣ ሙሉ ውለታው እንዲታወቅለት ይመስል ።

"ውይ በሞትኩት የኔ ጌታ ። አዪ ከሥራህ አስተጓጐልንሃ ። በጣም ነው የማመሰግነው" አሉ ፣ የምርም ነገሩ ከብዷቸው ።

"ኧረ ምንም አይደለም ። እደርሳለሁ ፣ ዛሬ ብዙም ከባድ ነገር የለኝም ። ወደዛ ወደ ካፌው ጋ ሄደን ሻይ እየጠጣን ብንጠብቅ ይሻላል መሰለኝ ። ዶክተር ሌላሠው የጠዋት ስብሰባውን ጨርሶ የሚወጣው ሦስት ሰአት አካባቢ ስለሆነ ብዬ ነው" አለ ። ተከታትለው ከሆፒታሉ የጐን መግቢያ አንጻር ከፊት ለፊት ከመንገዱ ዳር ወዳለችው ካፌ አመሩ ።

ነጫጭ የለበሱ ሃኪሞችና ነርሶች ቤቷን ሞልተዋታል ። ሁሉም በየፊናቸው እያወካኩ በሻይ ቡናው ዙሪያ ተጠምደው ገቢና ወጪውን ልብ የሚልም የለም ። በረንዳው ላይ ያልተያዘ ወንበር አገኙና ተቀመጡ ። አስተናጋጇን ደጋግሞ ምልክት ቢያሳያትም ችላ ያለችው ስለመሰለው በስጨት ብሎ አጨብጭቦ ጠራት ። የሰበሰበችውን ስኒዎችና ሰሃኖች እንደ ያዘች ፈንጠር ብላ ስትቀም ቀጣ ብሎ

"ቆይ ሁሌ መለመን አለባችሁ ማለት ነው? እስኪ ፈጠን ብለሽ ሦስት ማኪያቶ ... ኖርማል ... አሠሪልን" ብሎ ከመጨረሱ ፊቷን አዙራ ልትሄድ ስትል "እንዴ ... ምንድነው ነገሩ ዛሬ? ምን ያንቀለቅልሻል ... ምን ዓይነቷ ..." አለና ፣ ሊል ያሰበውን ዋጥ አደረገው ።

ራቅ ብላ የቀመችው አስተናጋጅ ደንታም እንዳልሰጣት ፣ "በቃ ... አዘዛችሁ አይደል? ..." አለችና ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች ።

"እንዲያውም ተዪው ... ተዪው በቃ ሂጂ ። ይቅርታ ስትክፍለፈለፍብኝ እኮ ምን እንደምትፈልጉም ሳልጠይቃችሁ ። ምን ይምጣላችሁ?" አለ ፣ በልጅቷ ሁኔታ በስጨት ብሎ ። ሁለቱም ማኪያቶው እንዲሆንላቸው ሲስማሙ ፣ በንዴት ፈንጠር ብሎ ተነሳና ዝም ብሎ አልፏት ወደ ውስጥ ገብቶ ተመለሰ ።

"አንጀት አድብን ብቻ እኮ ነው የተሰበሰበው ። ከየት እንደሚለቃቅሟቸው አላውቅም ። ትንሽ ከተሻለ ብዬ ፣ ውስጥ ራሴ ለባሬስታው ነገሬው መጣሁ ። ያው መቻል ነው እንግዲህ ፣ የዚህ ቤት ማኪያቶ እንደ ካልዲስና ቶሞካ አይሆንም" አለ ፣ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ተቀመጠና ሳቅ ለማለት እየሞከረ ።

"ሻያቸው ግን ጥሩ ነው መሰለኝ ..." አለች ፣ ምስጢር የቡናው መራራ ጣእም ትዝ እያላት ።

አንዴ አካባቢውን አንዴ ሲራክን ሲያጤኑ የነበሩት የምስጢር እናት ፣ "አይ እንግዲህ ቤት ያፈራውን ነው ። አትቸገር ፣ ችግር የለም" አሉ ። የለበሰው ጥቁር ቡኒ ሙሉ ልብስ ከፈዛዛ ብርቱካንማ ሸሚዙ ጋር ጠይም መልኩን ፈካ አድርጎታል ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

የሲራክ ትልቅ ወጪው ቀበቶና ጫማው ነው። መናኛ ቀበቶና ደካማ ጫማ የወንድ ልጅን ቁመና በግማሽ ይቀንሳል የሚል አባባል አለው። በረጅም ቀጫጭን ቁመቱ ላይ ሁልጊዜም ጢሙን ሙልጭ አድርጎ ተላጭቶ ጸጉሩን አጎፍሮ ዘንከት ዘንከት ሲል ገና የኮሌጅ ተማሪ ይመስላል። ለደረሰበት የትምህርት ደረጃ ልጅ እግር መስሎ ታያቸው። ሁሌም ቀልባቸው የወደደውን ሰው ሲያዩ ለልጃቸው ማሰብ መሰለላቸው አይቀርም። በወሬ በወሬ ስለ ዶክተር ሌላው ኢንተርቪው አንስተው ሲጫወቱ ቀዩና ሲራክም ስለርሱ ስለሚያውቀው አንዳንድ ነገሮች አድንቆ ነገራቸው።

ብዙም ሳይቆይ የጠዋት ስብሰባቸውን ጨርሰው ዶክተር ሌላው ከሌሎች ሁለት ሳይካትሪስቶች ጋር ወደ ካፌው ሲገባ ከሲራክ ጋር ተያዩ። አብረው ያሉትን ሃኪሞች ይቅርታ ጠይቆ ሰላም ሊላቸው ወደ እነርሱ ጠርጴዛ መጣ። ምስጢርና እናቷም ደንገጥ ብለው ብድግ ብድግ ሲሉ፣ "እ-ን-ዴ ኧረ አይገባም። ተቀመጡ ... ተቀመጡ። ደህና አደራችሁ? ዶክተር ሲራክ፣ እነሱ ናቸው ዘመዶችህ?" ብሎ በሙሉ ፈገግታ አንዴ እርሱን አንዴ እነርሱን እያየ እጁን ለሰላምታ ዘረጋ።

"አዎን እነሱ ናቸው። እሳቸው እናቷ ናቸው። እሷ ናት እዚህ እኛ ጋ ለፐራክቲከም ባለፈው መጥታ ነበር ያልኩህ። የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ማስተርስ ተማሪ ናት" ብሎ፣ የቻለውን ያህል የማስተዋወቅ ሥራውን ለመሥራት ሞከረ። የምስጢርን እናት ሰላም ካለ በኋላ እሷን ሰላም ሊል እጁን ዘረጋ። "ሚስጥር" ስትለው ስሟን እንደነገረችው የተረዳው ተለይቷቸው ከሄደ በኋላ ነበር።

ሌላው ከካፌው ሲወጣ ሊመጡ እንደሚችሉ ለሲራክ በምልክት ስለ ነገረው ተከታትለው ወደ ክሊኒኩ አቀኑ። ካርድ እስኪያወጡ እንዲጠብቁ እናቷን ከቢሮው ፊት ለፊት ካለ አግዳሚ ወንበር ላይ ትተዋቸው ምስጢርና ሲራክ ወደ ካርድ ክፍል ሄዱ። የክሊኒኩ ኮሪደር ቀስ ቀስ እያለ በሰው መጨናነቅ ጀምሯል። በየቢሮው በራፍ ላይ የተኮለኮሉ ህመምተኞች፣ የቀጠሮ ክፍሎችን በራፍ ያጨናነቁ ተመዝጋቢዎችና የክሊኒኩ ሰራተኞች ሁሉም በየራሱ ጉዳይ ተጠምዷል።

ሌላው እንደ ለመደው ከሲስተር ዘቢባ ጋር ትንሽ ተጨዋውቶ ከነርሶቹ ቢሮ ሲወጣ የምስጢርን እናት በወረፋ መጠበቂያ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠው አየና፣ "ብቻዎትን ትተዎት የት ጠፉ?" አለ፣ ከአጠገባቸው ቀም ብሎ።

ተርበትብተው ከተቀመጡበት ብድግ እንደ ማለት ብለው፣ "ካርድ ሊያወጡ መሰለኝ፣ አሁን ነው የሄዱት ዶክተርዬ" አሉ፣ ውጪ ውጪውን እያዩ።

"ታዲያ እነርሱ እስኪመጡ ለምን እኔ ቢሮ ገብተን እየተጫወትን አንጠብቃቸውም? እንደሱ ይሻላል መሰለኝ" ብሎ፣ ቢሮውን ከፍቶ ቀድሞ ገባና ወንበሮቹን አስተካክሎ እንዲቀመጡ ከፊት ለፊት ያለውን ወንበር ጠቆማቸው። ከጠረጴዛው ጀርባ ባለው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ የተበታተኑ ወረቀቶችን እያስተካከለ፣ "ይቅርታ፣ ስምዎን ማን ነበር ያሉኝ? ቅድም እኮ ግርግር ሆኖ

Brought to You by t.me/bookshelf99

በደንብም አልሰማሁዎትም" አለ ፣ ቀና ብሎ ፊታቸውን በጥልቀት እየቃኘ ።

"አይ ዶክተር እናንተማ የስንቱን ሰው ስም ይዛችሁ ትችሉታላችሁ ። ኤደን እባላለሁ ። በጣም ነው የማመሰግነው መቼም ዶክተር ሊያዩኝ ፈቃደኛ ስለሆኑ ። አውቃለሁ ስራ በጣም እንደሚበዛብዎ" አሉ ፣ እጃቸውን እያፍተለተሉ ።

"ኧረ ደስታዬ ነው ። ምንም አይደል ፤ ደግሞ አንተ ይበሉኝ ። አንቱታው አይገባም" አለ ፣ በደማቁ ፈገግ ብሎ ።

"ያው ዶክተርንና ቄስን አንቱ ማለት የተለመደ ሆኖ ነው ። እሺ ፣ አንተ በዪኝ ካልክ ። ሰሞኑን በቴሌቪዥን የነበረህን ቃለ መጠይቅ ሁሉ ተከታትያለሁ ። መቼም ቃል የለኝም ፣ በጣም አስተማሪ ነበር ። በጣም ጥሩ ነው ። ለብዙ ሰው የሚጠቅም ነገር ነው" አሉና ብዙ እንዳያወሩ ለመቆጠብ ይመስል ከጎናቸው ያለው ወንበር ላይ ያስቀመጡትን ቀይ ቦርሳ አንስተው ታቀፉና ሳይታወቃቸው ሞምድድ አድርገው ያዙት ።

"ኦህ እውነት ፣ ተከታትለውት ነበር? እንዴት ነው ... አሳቡ ግን ግልጽ ነበር? አንዳንዴ የሕክምናና የሥነ ልቦናን ጉዳይ ባማርኛ ማብራራት በጣም ይከብዳል" አለ ፣ ፊቱ የበለጠ በርቶ ።

"ኧረ በጣም ግልጽ ነው ። እንዲያውም ልጄ ካአሜሪካ ነው ከጎንደር የመጣው ብላ ስትቀልድብህ ነበር ፤ ባማርኛህ እየተደነቀች" አሉ ፣ ፈገግታቸውን አስቀድመውና አነጋገራቸው መዳፈር እንዳይሆንባቸው በመፍራት ሰቀቅ እያሉ ። ለቀቅ ብሎ በደማቁ ሳቀና

"አ...ይ የጎንደሬ ያህል አማርኛ ማውራት ከቻልኩማ ፣ ጎበዝ ሆኛለሁ ማለት ነው ። እርሷ ብቻ ናት ወይስ ሌሎችም ልጆች አለዎ?"

"አይ እሷው ናት ። እንዴት ዓይነት የተባረከች ልጅ መሰለችህ ። ለሰው አዛኝ ፣ በዛ ላይ ስማርት የሆነች ልጅ ናት ። ይሄው አባቷ ከሞተ አሁን ሰባት አመቱ ሊሆን ነው ። እሷው ናት ቢዝነሱን ሁሉ ቀጥ አድርጋ የምታስተዳድረው ። በዛ ላይ ትምህርቷንም ጥሩ ይዛለች ። እንደ እናንተው ለመሆን ነበር ምኞቷ ፣ ማስትሬቷን በማማከር ከስድስት ኪሎ አሁን ሰኔ ላይ ትጨርሳለች ። ከተባረከ አንድ ልጅም መድሃኒት ነው" አሉ ፣ ፊታቸው ባንዴ እየፈካ ።

"ልክ ነው ። የተባረከ ልጅ አንድም ቢሆን በምንም አይለካ ፤ እድለኛ ነዎት" አለና ጉሮሮውን ጠረግ ጠረግ አድርጐ "በጣም አዝናለሁ ስለ ባለቤትዎ ። ብዙ ታመው ነበር?"

"አዎን ፣ ለረጅም ጊዜ ታሞ ነበር ፣ ከሁለት አመት በላይ ካልጋም ሳይወርድ ብዙ ስቃይ ውስጥ ነበር ። ጉበቱ ከጥቅም ውጪ ሆኗል ነበር ያሉት ሐኪሞቹ ። ታሪኩ ረጅም ነው ። እንዴት ያለ ጎበዝ የቢዝነስ ሰው ነበር መሰለህ" ሲሉ ፣ እንዲቀጥሉ

Brought to You by t.me/bookshelf99

በማደፋፈር አይነት ሜንቅላቱን እየነቀነቀ ዝም አለ ።

"እና የመጨረሻው የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት እስኪቀሰቀስ አስመራ ነበር የምንኖረው ። ታውቅ እንደሁ እንጃ ያኔ እዚህም እዛም ያሉ ብዙ ሰዎች ንብረታቸው መና ሆኖ ቀርቶ ነበር ። እኛ ደግሞ ምጽዋና አስመራ ላይ ብዙ ንብረት ነበረን ። ሁሉም ቀልጦ መና ቀረ ። እሱም በዛ ብስጭት መጠጣት ሆነ ሥራው ። ለነገሩ ባይልለት ነው እንጂ ገንዘብስ አልነበረም ችግሩ ። እዚህም የተሳካ ቢዝነስ ነበረው ። ግን በቃ ልቡም ነፍሱም እዛ የነበረው ሥራው ላይ ስለነበረ ፣ ነገሩ ሲበለሻሸበት ህልሙም አብሮ ሞተ መሰለኝ ። እያደር ብስጭቱም መጠጡም ተጨምሮ ጉበቱ በጣም ተጎዳ ። በኋላማ ሆዱ ውሃ እያጠራቀመ መንቀሳቀስም አቃተው ። ካልጋም ሳይወርድ ነው በዛው የቀረው" አሉ ፣ ቀስ በቀስ የሃዘን ድባብ ሲያጠላበት የነበረው ፊታቸው በእንባ እየረጠበ ።

ከፊት ለፊቱ ያለውን ናፕኪን ሲያስጠጋላቸው ፣ "ኧረ እዚህ ቦርሳዬ ውስጥ ሳይኖረኝ አይቀርም ። ይቅርታ ፣ እንግዲህ ገና ከመግባቴ አንተንም አስቸገርኩሀ" አሉ ፣ እንባቸውን ከቦርሳቸው ባወጡት ነጭ መሃረብ ጠረግ ጠረግ እያደረጉ ።

"ኧረ በፍጹም አይጨነቁ ። አዝናለሁ ..." ብሎ ፣ ስሜታቸው ተረጋግቶ ለመመለስ እስኪዘጋጁ ትንሽ ዝም ብሎ ቆየና 'አስመራ ብዙ ኖራችሁ ነበር?" አለ ረጋ ባለ ድምጽ ።

"እኔ ያስመራ ልጅ ነኝ ። ከሱ ጋራም የተገናኘነው ደርግ ከመውደቁ አስር አመት በፊት እዛው ነበር ። በሙያዬ አካውንታት ስለነበርኩ አንዳንድ ሥራ እሠራለት ነበር ። ያው መቼም የፈጣሪ ፈቃድ ከማን እንደሚያጣምርህ አታውቀውም ። ሚስጥርዬም እዛው ነው የተወለደችው ። ደርግ ሲወድቅ የነበረው ግርግርና ችግር መቼም ካቅም በላይ ነበር ። ብዙ ሰው ተበተነ ፤ ስንቱ ተፈናቀለ መሰለህ ።

"ባለቤቴ ግን በቃ ከሰዎቹ ጋር በጣም ይግባባ ስለነበር ምንም አልተቸገርንም ። ደርግ ሳይወድቅ በፊትም በገንዘብ ይደግፋቸው ስለ ነበር ፣ በነጻነት ማግስት ማንም አልነካውም ። ከወደዱህ እንዴት ጥሩ ሰዎች መሰሉህ ። ይገርምሃል እሱ የመሃል አገር ጉራጌው ከኔ ከአስመራዊቱ ይልቅ የአገሬው ሰው ሆኖ ነበር ። በኋላ ግን ይሄ የመጨረሻው የድንበር ግጭት ሲነሳ ነገር ሁሉ ተቀያየረ ። የሚጠሉት ሰዎች ጥሩ አጋጣሚ አገኙ ። የሆነ ያልሆነ ነገር አስወርተው ችግር ውስጥ ከተቱት ። ደግሉ ሰው ስለሚወደውና ብዙ ሰው ስለሚያውቅ ንብረት ቢጠፋም እኛን ግን ምንም ሳንሆን በሰላም ወደዚህ ሸኙን" ብለው ፣ የሃሳባቸው ውል የጠፋቸው ይመስል ዝም አሉ ።

"እዚህ ከመጣችሁ በኋላ ያጋጠማችሁ የተለየ ችግር ነበር? ማለቴ ከነገሩኝ ነገር ሌላ የባለቤትዎን ጸባይ እንዲቀየር ያደረገው ነገር ካለ ብዬ ነው?" አለ ፣ አሁንም እርሱን ለማየት ያመጣቸውን ችግር ከመጠየቁ በፊት ቀደምት ታሪካቸውን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ማጣራቱን መርጦ ።

ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ቀዩና ፣ "ያው የሱ ዘመዶች መሀል ምንም ሰላም የለም ። እንዴት መሰለህ ... አባቱም በጊዜያቸው የተሳካላቸው ነጋዴ ነበሩ ። ከልጆቻቸው ሁሉ እሱን ነበር በጣም የሚወዱት ። እናቱ ቀድመው ሞተው ስለ ነበር ትልቅ ግቢ ያለውን ዋናውን መኖሪያ ቤታቸውንና አብላጫውን ንብረታቸውን ለሱ ነበር ያወረሱት ። በዚያ የተነሳ ቤተሰቡ ውስጥ ብዙ ብጥብጥ ተፈጠረ ፣ ሁሉም ተባብረው አደሙበት ። ያ በጣም ያበሳጨው ነበር ። ብቻ ወደ እዚህ ከመጣን በኋላ ከሰዉ ሁሉ ጋር መስማማት አቃተው ።

"እንደ መሰለኝ ብዙ ያመናቸው ጓደኞቹም ገንዘብ እየተበደሩት ሳይከዱት አልቀሩም ። ብቻ መጨረሻ ላይ ብስጭትና መጠጣት ሆነ ሥራው ። እያደርማ ጭራሽ ኑሮውን በየቡና ቤቱ አደረገ ። ሰክሮ ወደ ቤት ሲመጣ ደግሞ እኛንም ሰላም ይነሳን ጀመር ። መጀመሪያ ላይ ስድብና ጩኸት ነበር ። እያደር ግን ዱላና አምባጓሮ ሁሉ አመጣ ። እኔም ሲያቅተኝ ቤቱን ጥዬ ወጥቼ ነበር ለተወሰነ ጊዜ ..." አሉና ስቅስቅ ብለው ሲያለቅሱ ፣ የሚያደርገው ስለ ጠፋው ለትንሽ ጊዜ በዝምታ ጠበቀ ።

በየመሀሉ "በጣም አዝናለሁ ..." ብቻ እያለ ፣ ስሜታቸው እስኪረግብ ድረስ በዝምታ ጠበቃቸው ።

የለቅሶው ሳግ ትንሽ ተንፈስ ሲልላቸው ፣ "ነገሩ በጣም ምርር ሲለኝ ቤቱን ጥዬ ወጣሁ ። ያኔ ታዲያ ሚስጥርዬን ከሱው ጋር ነበር ትቻት የሄድኩ ። ከእኔ ጋር እንዳትንገላታ ነበር የኔ አሳብ ። እንደው እግሬን በሰበረው ያኔ ..." አሉና አሁንም ሌላ ዙር ለቅሶ ማልቀስ ሲጀምሩ ይበልጥ ግራ ገባው ።

ከመቀመጫው ተነስቶ አጠገባቸው ተቀመጠና እጁን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርጎ ደጋግሞ ፣ "አይዝዎት ..." እያለ ከውስጣቸው እየፈነቀለ የሚፈልቀው ትኩስ እምባ ጋብ እስኪልላቸው ጠበቀ ።

"መጀመሪያ ላይ ሰክሮ ይመጣና እኔን ሲሰድበኝ ወይ ሲደበድበኝ እሪ ብላ ስታለቅስ ይጮህባታል ወይ በጥፊ ብሎ ከአጠገቡ ያባርራታል ። አንዳንዴ ደግሞ ጥንብዝ ብሎ ይመጣና አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ሲጮህ ይቀይና ተነስቶ ሳሎን ሶፋ ላይ ተጋድሞ ያድራል ። እኔ ቤቱን ጥዬ ስሄድ እሷ ከርሱ ጋር ለመቀየት መርጣ ስለነበር ትቼያት ነበር የሄድኩት ። ምን እንደሆነችም አላውቅም ፣ ብዙም ሳይቀይ እሷም ቤቱን ጥላ አክስቷ ቤት ገባች ። ከዛ በኋላ ታሞ አልጋ ላይ ሲወድቅ ታረቅንና ተመልሼ ገባሁ ። እሷ ግን ሊሞት ጥቂት ቀን እስኪቀረው ድረስ ፊቱንም አላየችውም ።

"በጥፋቱ ጸጸት ይሁን የዘመዶቹን ክፋት ስለሚያውቅ እንጃ ፣ ያለውን ሃብት ሁሉ ገና በህይወት እያለ ነበር በስሟ ያዞረው ። ሊሞት ሳምንት ሲቀረው ብቻ በስንት አማላጅ መጥታ አየችው ። 'ልጄ ምነው ስቃዬን አይተሽ እንኳ ይቅር ብትይኝ...'

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሲላት ‘አንተ አውሬ ነህ ... ይቅርታ አይገባህም ፣ የሚገባህን ነው ያገኘኸው’ ብላ ጥላው ሄደች ። ላየዋን ስታየው ገርና ሳቂታ ትመስልሃለች እንጂ ውስጧ ያልበረደ ቁጣ እዝላ ነው የምትዞረው” ብለው ፣ በጫማቸው መሬቱን እየቀረቀሩ አቀረቀሩ ።

በግራ እጁ መላ ፊቱን አሻሸና የእጆቹን ጣቶች እርስ በርስ አቆላልፎ፣ “በጣም ከባድ ነገር ነው ... ” ብሎ ዘለግ ላለ ቅጽበት ሁለቱም ዝም ብለው ቀዩ ። ጸጥታው የጨነቃቸው ይመስል ትንሽ ትንፋሻቸውን ዋጥ አደረጉ ። የተነሱበትን ሃሳብ ለቀው ብዙ እንደ ሄዱ ሲገባቸው አፈር ብለው ዝም አሉ ። የልጃቸውን የግል ጉዳይ ገና በመጀመሪያ ቀን ማውራታቸውም ሀሊናቸውን ሸንቁጦት እንደገና እግር እግራቸውን እያዩ አቀርቅረው ቀሩ ። ነገሩ የገባው ይመስል ትንሽ ሃሳባቸውን መሰብሰብ እንዲችሉና ስሜታቸው እንዲረጋጋ ቀለል ያሉ ጉዳዮችን ሲያወራቸው ቀየ ። ሙሉ ለሙሉ ሲረጋጉ እሱን ሊያዩ ስለ መጡበት ጉዳይ እንዲነግሩት ጠይቋቸው ወደ ወንበሩ ተመለሰ ።

“ምኑን ነግሬህ ምኑን ልተወው ዶክተር?” ብለው ፣ መነሻና መድረሻው እንደ ጠፋባቸው መሬት መሬቱን ሲያዩ ቆዩና የተከፈተ ቦርሳቸውን ዘግተው አጠገባቸው አስቀመጡት ። “ትልቁ ችግር ... ስንት ጊዜዬ መሰለህ ዶክተርዬ ፣ የረባ እንቅልፍ ባይኔ ከዞረ ። ደግሞ በቃ በሆነ ባልሆነው ሆድ ይብሰኛል ። ሰው ማግኘትማ ገና ላስበው ያደክመኛል ። ጨለም ያለ ቦታ ሆኜ ስተክዝና ስቀዝም ለብቻዬ ቁጭ ብዬ መዋል ነው የምመርጠው ። ጠዋት ሲነጋ ካልጋ መውጣት ስቃይ ነው ። ልክ በቃ ሌሊቱን ሁሉ ከባድ ሥራ ሲሠራ እንዳደረ ሰውነቴ ሁሉ ዛል ብሎ ጉልበቴ ፍስስ ብሎ ነው የምነሣው ። የሌሊቱ መላ ቅጥ የሌለው ቅዠት ሳያንስ ቀኑን ሙሉ ደግሞ የሆነ ያልሆነው ነገር እንደፊልም ፊቴ ደንቅሮ ሲያጫውተው ይውላል ። በር ሲዘጋ ወይ የሆነ ነገር ወድቆ ኳ ያለ እንደሆን ፈንጂ የፈነዳ ያህል መዝለል መደንበር ነው ።

“ምንም የገደለ ነገር ሳይኖር በሆነ ባልሆነው ነገር መጨነቅ መጠበብ ነው ። አንዳንዴማ በቃ ልቤ ድንገት ተነስታ በጉሮሮዬ ልውጣ ትላለች ። ትንፋሽ አጥሮኝ ከላይ ከላዩ ስተነፍስ ያስለመልመኝና ያለሁበትንም አላውቅ ። ከዛ ሰውነቴን ሞምድድ አድርገኝ ይቀይና ድንገት ቀዝቃዛ ውሃውን ጀርባዬ ላይ ይከልሰዋል ። ሰውነቴ ሁሉ በድን ይሆንብኝና የኔም አይመስለኝም ። ኧረ ስንቱን ልንገርህ ዶክተር” ብለው ፣ ሞንቅ እንዳላቸው በመስኮቱ አሻግረው እያዩ ዝም አሉ ።

“ከዚህ በፊት ሃኪም ወይም አማካሪ ጋ ታይተው ያውቃሉ?” ብሎ ፣ የነገሩትን ሰፊ የስሜት ስቃይ ዝርዝር ማሰብ ቀጠለ ። በእንቅልፍ እጦት የጠቆረው የዓይናቸው ዙሪያና ድርብርብ ሞንቀት የረበበበት ፊታቸውን ሲያይ የዘረዘሩት የውስጥ ስቃይ ገጻቸው ላይ የተጻፈ መሰለው ።

“አንድ ሁለቴ ታይቼ ነበር ፣ እዚህ ምንድነው ስሙ እቴ? የግል ክሊኒክ ነው ። ምንም አልረባኝም እንጂ ፣ አንድ ሁለት የሚሆን መድሃኒትም ሰጥተውኝ ነበር ። ይሄውልህ በቃ ትንሽ ትልቁን ሁሉ መርሳት ነው ። እንዲየው ምን ይሻልኝ ይሆን?

Brought to You by t.me/bookshelf99

የሰጡኝ መድሃኒትም ቢሆን ማፍዘዝ ማስተኛት ካልሆነ ምንም አልፈየደልኝም ። እንድ ስድስት ወር ሞክሬ ተውኩት ። ከዚያም ጠበሉንም ፣ የባህሉንም መድሃኒት ፣ ሁሉንም ሞክሬ ነበር ። ጊዜ ሰጥቶ የሚያዋራ ሁነኛ አማካሪ ማግኘቱ ደግሞ ከባድ ነው" ብለው ፣ በረጅሙ ተነፈሱ ።

"ቅድም በእንቅልፍ ተኝተው በቅዠትና ቀንም ነቅተው እያሉ ትዝታው ፊቴ ላይ እየመጣ ያስቸግረኛል ያሉኝ ነገር ነበር ። ነገሩ ከዚህ ቀደም በህይወትዎ ከደረሰ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው?" ሲል ፣ ጥቂት ጸጥ ብለው ቆዩ ። ድንገት ኩልል ብሎ በጉንጫቸው ላይ መፍሰስ የጀመረውን እምባ በመዳፋቸው ጠረግ አደረጉና ፣

"አ-ባ-ቴንና ወን-ድ-ሜን ዓይኔ እያየ ነው የገደሏቸው ። ሻእቢያ ናቸው ብለው ደጃፋችን ላይ ደፍተዋቸው ሄዱ ። እኔ ያኔ ወጣት የኮሌጅ ተማሪ ነበርኩ ። ታናሽ ወንድሜ ብቻ ሸሽቶ ወደ ጫካ ገባ ። እኔም ብዙም ሳይቆይ እስር ቤት ተወሰድኩ ። ወንድምሽ የት እንዳለ ምረ ፣ የኩተማ ሰላይ ነሽ ተብዬ የደረሰብኝን ግፍና ስቃይ በቃላት ልነግርህ አልችልም ። እናታችን ብቻዋን ቀርታ እንዲሁ በሃዘን እንደተቀራመዶች በዓመቱ ሞተች ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከእስር ቤት ስወጣ ህይወቱ ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ ነበር ።

"ይሄንን ሁሉ ጉድ ደህና የረሳሁት መስሎኝ ነበር ። የጠፋ የመሰለኝ ነገር ሁሉ አሁን እንደ ተቀበረ ፈንጂ መፈንዳት ሲጀምር ውስጤን እያፈራረሰው ነው ። አሁን ከስንት ዓመት በኋላ እንደ አዲስ ነጋ ጠባ እነሱ ናቸው ፊቴ ላይ የሚመጡት ። ልክ ትናንት የሆነ ነው የሚመስለኝ ። በቃ መተኛትም ብቻዬን መሆንም እንዴት እንደሚያስፈራኝ አትጠይቀኝ ። በተለይ ያባቴና የወንድሜ ፊታቸው ላይ የነበረው ስቃይ ፊቴ ድቅን ይልብኛል ። እስር ቤት የደረሰብኝ ግፍ ...ግርፋቱ ... መደፈሩ ... እህ...ህ...ህ" ብለው ፣ ልክ አሁን የሆነ ያህል ሰውነታቸው ተንዘፈዘፈ ። በዚህ ጊዜ አባቱ የጻፉለት የኑዛዜ ደብዳቤ ትዝ አለው ። ምንም የሚለው አልነበረውም ።

"አንዳንዴ ሌሊት በቅዠት ስጮህ ሰምታ ልጄ ትመጣና ስትቀሰቅሰኝ ላብ በላብ ሆኜ ታገኘኛለች ። ከዛ በኋላ ተመልሼ መተኛትም ስለምፈራ ቁልቁሉ እንዳልኩ ይነጋል ። ቀኑን ደግሞ በእንቅልፍና በጎታት መካከል ሆኜ ወይ ሲያንገላጅጀኝ ያልፋል ፣ አለበለዛም በቃ ሶፋው ላይ ደገፍ ባልኩበት ትንሽ ያሸልበኛል ። ሜንቅላቴ ያንኑ መልሶ መላልሶ እንደ ፊልም ሲያሚወ-ትብኝ ይው-ላል ። ዶክተርዬ እንዲህ ስታየኝ ደህና እመስልሃለሁ እንጂ ፣ ተሸክሜ የምዞረው ጉድ እኮ ማለቂያም የለውም ። ሰው በቀን እረፍት ፣ በማታ እንቅልፍ ሳይኖረው እንዴት ይኖራል?" ብለው ፣ ዓይናቸውን በያዙት መሃረብ አደራረቁ ።

" በጣም አዝናለሁ ወይዘሮ ኤደን ፣ በጣም ከባድ ነገር ነው ። "

እጁ ላይ ያለውን እስክርቢቶ በጣቶቹ እያፈተለተለና ፊታቸውን እያጠና 'እንዴት አንድ ሰው ይሄንን ሁሉ መከራ ይቀበላል ፣ እንዴትስ ይሄንን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሁሉ ጉድ ተሸክሞ ሊኖርና ቀሞ ሊሄድ ይችላል?' የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያስብ ቀየ። ምናልባትም ረጅም ጊዜ የሚወስድ የምክክርና የመድሃኒት ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው ገመተ። የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜም ስለሆነ ለዛሬ እስካሁን ከነገሩት ታሪክ በላይ መሄድ አልፈለገም።

ጥቂት የቀሩ መሰረታዊ ነገሮችን ከጠየቃቸው በኋላ ሰአቱን አየት አድርጎ ክፍሉ ውስጥ የሰፈነውን ከባድ የሃዘን ስሜት ለማርገብ፣ "እነዚህ ልጆች ካርድ ለማውጣት ተቸግረው ይሆን እንዴ?" ብሎ፣ ስልክ ለመደወል ከኪሱ ሲያወጣ በሩ ተንኳኳ። ሲስተር ዘቢባ ነበረች።

አንገቷን በከፊል አስገብታ፣ "ይቅርታ ዶክተር ካርዱ ወጥቷል። እነ ዶክተር ሲራክ እኮ ከመጡ ቆይተዋል። እንዳያቋርጧቸው ብለው እኔ ቢሮ ነው ያሉት። ድንገት ካርዱን ከፈለግኸው ብዬ ነው" አለች።

"አይገርምሽም እኛም ካርዱን ለማውጣት አስቸግሯቸው ይሆን ብለን ልክ ልደውልልሽ ስል ነው የመጣሽው። ታንክ ዩ ሲስተርዬ።" ካርዱን እየተቀበላት ወደ ምስጢር እናት ዞር ብሎ፣ "ልጅዎት አሁን ብትገባስ? እኛ ለዛሬው ምናልባት ላይበቃን አይቀርም" አለ።

ወይዘሮ ኤደንም ፈጠን ብለው፣ "አዎን፣ ጥሩ ነው። ጥሩ ነው፣ ትግባ" አሉ፣ ሽቁጥቁጥ ባለ ድምጽ።

"በቃ ልጃቸውም ትግባ፣ ንገሪያት ሲስተርዬ" አለ፣ የተቀበላትን ባዶ ካርድ ከፍቶ ከፊቱ እየዘረጋ። ሲስተር ዘቢባ በሩን ዘግታ ስትሄድ ወደ እርሳቸው ዞር ብሎ፣

"ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ያህል የምክርና የመድሃኒት ህክምና ማድረግ ያስፈልግዎ ይሆናል። ያለፉበት ነገርና አሁንም የሚሰማዎ የስሜት ስቃይ ከፍተኛ ስለሆነ ሙሉ ለሙሉ እስኪሻልዎ ረዘም ያለ ጊዜ ቢወስድም መታገስ ያስፈልግዎታል። እኔም እንግዲህ ከእግዜር ጋር የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። መርሳት የሌለብዎ ነገር ግን ይህንን ሁሉ ፈተና አልፈው ዛሬ ላይ መቀምዎ ራሱ የሚያሳየው፣ ምን ያህል ከባዱን ሥራ በራስዎ እንዳለፉት ነው። ስለዚህ በፍጹም ተስፋ መቁረጥ የለብዎትም" ሲል፣ ሞንቅላታቸውን በአዎንታ በመነቅነቅ መስማማታቸውን ገለጡ። ወዲያው በሩ ተንኳኳና ምስጢርና ሲራክ ተከታትለው ገቡ።

"እኛ ኮ ካርድ አልቆ ለፍለጋ ወደ ከተማ ሄደው ይሆን ብለን አሳብ ገብቶን ነበር" ሲል፣ ሁሉም ሳቁ።

"ኧረ ወዲያው ነበር እኮ የመጣነው። ላለመረበሽ ብለን እነ ሲስተር ዘቢባ ቢሮ ተቀምጠን ነው" አለ፣ ሲራክ እንደ ቀሙ እጁን እያሻሸ።

"አይ ቀልዴን ነው፤ ሲስተር ነገረችን እኮ። ቁጭ አትሉም ታዲያ?" አለ፣ ወደ ባዶ ወንበሮቹ እየጠቆመ ሁለቱንም በመጋበዝ፣

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አይ ዶክተር፣ እኔ እንኳ ብሄድ ይሻላል። አማኑኤል ከምሳ በፊት የምደርስበት ጉዳይ አለኝ። የሚሰጥርን እናት ሳልሰናበታቸው እንዳልሄድ ብዬ ነው የቀየሁት" አለ፣ ወደ እሳቸው ጠጋ እያለ።

"በጣም ነው የማመሰግነው የኔ ጌታ፣ አደከምኩህ ግን" አሉ፣ እየተሽቀጠቀጡ በሁለት እጃቸው እጁን እንደጨበጡ፣

"ዶክተር ሲራክ በጣም ገበዝ ሐኪም ነው። ትልቅ ተስፋ ከሚጣልባቸው ወጣት ዶክተሮቻችን አንዱ እሱ ነው" ብሎ፣ እርሱም ጨበጠውና "ነገ ጥቁር አንበሳ እንገናኝ የለ?" አለው።

"ልክ ነው፣ የከሰአት በኋላውን ሴሚናር አንተ ነህ አይደል የምትሰጠን?" አለ። ከመውጣቱ በፊት ዞር ብሎ ከናቷ ጐን የተቀመጠችውን ምስጢርን በእደውላለሁ ምልክት እጁን አሳይቷት በሩን ዘግቶ ወጣ። እሱ ከወጣ በኋላ ለጥቂት ደቂቃ ክፍሉ እንደገና ጸጥ ብሎ ቀየ። ሌላሠው አይኖቹን ምስጢር ላይ ጣል አድርጎ ረጋ ባለ አነጋገር፣

"ያው ከእናትሽ ጋር የተወሰኑ ነገሮችን ለማውራት ሞክረናል። ወዳሜሪካ ከመመለሴ በፊት የተወሰኑ ሳምንታት ብቻ ስለሚቀረኝ በሳምንት ሁለት ቀን ላያቸው ነው የተስማማነው። በቂ እንቅልፍ እንዲተኙና የሚሰማቸውን የጭንቀትና የውጥረት ስሜት ቶሎ ለማርገብ መድሃኒት ለተወሰነ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። አንቺም በቻልሽው መጠን ሥራዬ ብለሽ አብረሻቸው ብታሳልፊ ጥሩ ይመስለኛል" ሲል፣ በመስማማት ራሷን ነቀነቀች። እናቷ ቀበል አድርገው

"እሷማ መች ካጠገቤ ትለይና" አሉ፣ በስስት አይን እያዩዋት።

"ልክ ነው። እሱ እንደ እናትና ልጅ ሊሆን ይችላል፤ ግን ደግሞ ችግሩን እንደ ህመም አይቶ በማስታመምና በመደገፍ አንጻር ማለቴ ነው" አለና ሁለቱንም በተራ በተራ እያየ "ይሄ ካርዴ ነው፣ ምንም ችግር ካለ ደውሉልኝ። ወዲያው እንኳ ማንሳት ባልችል በቻልኩት ፍጥነት እመልሳለሁ" ብሎ፣ ሁለት ካርድ አወጣ። ምስጢር ልትቀበለው እጇን ስትዘረጋ በጣቶቿ መሃል ሾልኮ መሬት ወደቀባት።

"ኡፐስ ... ይ-ቅ-ር-ታ" ብላ፣ ከወደቀበት አንስታ ቀና ስትል ፈገግ ብሎ በምንም አይደለም አይን ሲያያት እንደ ማፈር ብላ አይኗን ሰበረች። ስለ መድሃኒቱ አወሳሰድና ዋና ዋና የጐን ጉዳቶች አስረድቷቸው ማዘዣውን ሰጣቸው።

ያቀረቡለትን ጥቂት ጥያቄዎች ከመለሰላቸው በኋላ ሊያሰናብታቸው ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ በሩ እያመራ፣ "ስለዚህ በቃ ሲስተር ዘቢባ ጋ ሂዱና ለሐሙስ ቀጠሮ ውሰዱ። ማክሰኞና ሐሙስ ጠዋት ከሶስት እስከ አራት ሰአት ጥሩ ነው?" አለ፣ በየተራ እያያቸው።

"በጣም ጥሩ ነው። ዶክተር መቼም ቃል የለኝም፣ እጅግ በጣም ነው

Brought to You by t.me/bookshelf99

የማመሰግነው" አሉ፣ እናቷ ። ምስጢርም መስማማቷን ገለጸች ።

እርሳቸውን ከተሰናበተ በኋላ ሲጨበጣት ፣ "ሚስጥር ... ቀንጅ ስም ነው" አላት ።

ፈገግታ ተሞልታ የስሟን ቃል ጎተት አድርጋ ፣ "አመሰግናለሁ ። ትክክለኛው ስሜ 'ሚስ-ጥ-ረ' ነው ። " አለች ።

የበለጠ ፈገግ ብሎ ፣ " ኦህ! ኢቫን ቤተር" አለና በራን ከፍቶ ያዘላቸው ። የእናቷ ትከሻ ላይ እጁን ጣል አድርጋ ተከታትለው ወጡ ።

የቀረውን ሙሉ ጠዋት አልፎ አልፎ 'ምስጢረ' የሚለውን ስም ትዝ ሲለው ዋለ ። ያላለቀ ፣ የተንጠለጠለና ያልረገበ በጅምር ተንጠልጥሎ የቀመ ሙዚቃ መስሎ ተሰማው ። የወይዘሮ ኤደንን ስቃዮች ሲያስብ ደግሞ ፣ ያለፉበት የሕይወት መራራና ጠመዝማዛ መንገድ የስንት ሰው ታሪክ ሊሆን እንደሚችል አሰበ ። አባቱ የጻፉለት የትዝታ ማስታወሻ ከነሙሉ ግዝፈቱ ለመጀመሪያ አፍጥጦ ታየው ።

ከርሱ ቢሮ ሲወጡ ምስጢር እናቷን ከሲስተር ዘቢባ ጋ አስተዋወቀቻቸው ። የሚቀጥለውን ቀጠሯቸውን አስመዝግበው ወደ መኪናቸው ሄዱ ። "እንዴት ነበር ማሚ? ምነው ብዙ አስለቀሰሽ እንዴ ፣ ፊትሽና ዓይንሽ?" ብላ ፣ የለበሱትን ጥቁር ያንገት ልብስ አስተካከለችላቸው ።

"ውይ ቢለቀስስ ደግሞ ፣ ብታዪ በጣም እንዴት አይነት ሩሀሩህ ሰው መሰለሽ ። ከማንም ጋር አውርቼው የማላውቀውን ጉድ ሁሉ ነው ማውራት የቻልኩት ። እንደ ሌሎቹ ዶክተሮች ተዋክቦ አያዋክብሽም ። ዝም ብሎ ሲያዳምጥሽ የሆነ ነገር ከውስጥሽ አውሪ አውሪ ያሰኝሻል ። ከኔ በቀር ሌላ ታካሚ ያለውም አይመስልም ። መናገር ራሱ ለነ መድሃኒት ነው ። ኡፍፍ ... እንዴት ቅልል እንዳለኝ ። "

"አምን ፣ ሥርዓት ያለው ሰው ይመስላል ። በሳምንት ሁለት ጊዜ ሊያይሽ መፍቀዱም ደስ ነው ያለኝ ። እኔ ምለው ግን ወላጆቹ ሌላሠው ያሉት ፣ የምር ሌላ ስም አጥተው ነው?" ብላ ሳቀች ።

"ምን ታውቂያለሽ? ያገራችን ሰው እንዲህ አይነት ስም ያለ ምክንያት አያወጣ ። ደግሞስ ጥሩ ስም ነው ፤ ምን ወጣው?" አሉ ። ነገር ስትፈላልጋቸው መሆኑን አውቀውታል ።

"እሱማ መጥፎ ስም ነው አላልኩም እኮ ፤ እንዲያው ገርሞኝ ነው ። ማለቴ ሲወለድ ምን አይነት ሰው ጠብቀው ቢሆን ነው? የምልሽ አይ አም ሹር እሱ ሲወለድ አልትራሳውንድ ምናምን አልነበረም ። ምን ያህል ከጠበቁት የተለየ ሀጻን ቢሆንባቸው ነው ሌላሠው ያሉት ብዬ ገርሞኝ ነዋ" ብላ ፣ አሁንም እንደ ሞኝ ስትስቅ ትንሽ እንደመናደድ አሉ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ጀመረሽ ደግሞ ይሄ ቂልነትሽ፣ ይልቁን ያ ያንቺ ጓደኛ ትንሹ ዶክተር ማነው ስሙ እቴ፣ ጥ...ሩ ልጅ ይመስላል። ቁም ነገረኛ ነው፤ እዚህ ድረስ ለኛ ብሎ መምጣቱ። ብዙ ትተዋወቃላችሁ?" አሉ፣ ነገሩን ለመቀየርም ትንሽም የማወቅ ፍላጐታቸው ተጨምሮበት።

"ሲራክን ነው? ረሳሽው እንዴ ... ነግሬሽ ነበር እኮ። ያኔ እዚህ ለፐራክቲክም የመጣሁ ጊዜ ጳውሎስ ነበር የሚሰራው። ትንሽ ችክ ያለ ቀበጥ ቢጤ ነው። ስለ ራሱ ያለው አመለካከትም ቁልል ተራራ ነው የሚያክለው። አለ አይደል፣ አፍቃሪ-ሲራክ ነገር ... ገባሽ አይደል?" አለች።

"አቤት አቤት አንቺ ልጅ፣ ኧረ እንዲየው ለሰውም ጡር አለው። እንዲያው ላንቺ ማን ይሆን ጥሩ ሰው? እንዲያው እሱ ብቻ ያሳየኝ ያንቺን ነገር" ብለው፣ ቦርሳቸውን ወደ ጎለኛው ወንበር ወርወር አድርገው ተመቻችትው ተቀመጡ።

የጉዞ ቀበቶውን እያጠበቁ በጐን አየት ሲያደርጓት፣ "ለኔ ጥሩ ሰው ይጠፋል ብለሽ ነው ማሚዬ፤ አንድ ቀን ይመጣል። አሁን ያሉት ግን ሁሉም ያው ሰው ነገር ናቸው። ሰው ነገር ደግሞ መች ጠፋ፣ በተለይ ወንድ። አታይውም መንገዱን፣ የታክሲ ውይይቱን፣ ቀበሌና ሱቁን፣ ቢሮውና እስር ቤቱን የሞላው ሁሉ ወንድ ነኝ ባይ ነው እኮ" ብላ፣ የመኪናውን የጣሪያ መስኮት ከፈተችው። "አገሩ ሁሉ ሰው ነው ... ሰው መች ጠፋ። እስካሁን ሊገኝ ያልቻለው ... ሌ...ላ... ሰ...ው ነው ማሚዬ" ብላ፣ የውሽት ስትስቅ በትዝብት ዓይነት ፈገግ ብለው የጐሪጥ አዩዋት። "ዶክተሩን ሌላሠው ማለቴ መስሎሽ ነው አይደል? ... አይ ማሚ ... እሱንስ ማን አየው ብለሽ ነው። እኔ በጠቅላላው ሌላ ሰው ማለቴ ነው። ደግሞ ... ለዚህ እኮ ነው ለምንድነው ሌላሠው ብለው ስም ያወጡለት ያልኩሽ" ብላ እንደገና ሳቀች። "ወደው አይስቁ" አሉና እሳቸውም ከት ብለው ሳቁ።

"ይልቁን ሚስጥሬ ሙች ያንን ትንሹን ዶክተር ቀልቤ አልጠላውም። ውይ ደግሞ እንዴት ሽር ሽቁጥቁጥ እንደሚልልሽ" ብለው ከዓይኗ ውስጥ አሳቢን ለመበርበር ይመስል አጥልቀው ሲያዩዋት፣

"አይ ማሚዬ ነገርኩሽ እኮ፣ ልጁ ብልጣብልጥ ነገር ነው። ሽቁጥቁጥነትና እሱ አብረውም አልተፈጠሩ። እዛ ካፌ ቅድም አስተናጋጇን እንዴት እንዳመናጨቃት አላየሽውም እንዴ? ከኔ የሆነ ነገር ባይፈልግ እንኳን በጠዋት ስራ ትቶ እዚህ ሊመጣ፣ አዪ ተይው ባክሽ፣ ተበልቶበታል። ትዝ አይልሽም እንዴ? ነግሬሽ ነበር እኮ። ያኔ እዚህ ስሰራ አላስቀም አላስቀምጥ ያለኝ እኮ እሱ ነበር። ደግሞ ከተማሪውም ከነርሱም ጋር ስለሚጓተት አይመስጠኝም" ብላ፣ መሪውን መታ አድረገች።

ሳታስበው ፍጥነቷን ጨምራ ኖሮ፣ "ኧረ ልጄ ቀስ በይ... የት ለመድረስ ነው? ግን ደግሞ ዶክተር ሌላሠውስ ቢሆን እንዴት አድንቀት እንደተናገረ አልሰማሽም?" አሉ ተስፋ ባለመቁረጥ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

ትንሽ በስጨት ብላ፣ "ማ-ሚ ደግሞ፣ እሱ የዶክተር ሌላው ምርጫ ነው። ከሜሪካ የመጡ ሰዎች ደግሞ የለበጣ ማቀላጸስ የማልወደው ጸባያቸው ነው። የምሩንም ላይሆን ይችላል። ይልቁን ሲራክን እንርሳውና እስኪ ኤንሪኮ ገራ እንበል? እኔ ኬካቸው አምሮኛል" አለች ድንገት ፊቷ በርቶ። የጣፋጭ ነገር ጠር ናት።

"ጥሩ ነዋ... ካላለቀ... አራት ሰአት ተኩል ሆኗል ግን" አሉ ሰአታቸውን እያዩ።

"እንሞክር ዕድላችንን" አለችና ወደዛው አመሩ።

ሲደርሱ ኤንሪኮ እንደ ልማዱ ገና በረፋዱ በሩን ዘግቶ ጠበቃቸው። በአራት ኪሎ ውስጥ ለውስጥ አቋርጠው በፍጥነት ወደ ቤት ነዱ። እንደ ደረሱ ምስጢር ድክም ስላላት ቁርስ ቢጤ ቀማመሰችና ትንሽ ለማረፍ ስለፈለገች አልጋዋ ላይ ጋደም አለች። በተከፈተው መስኮት አሻግራ፣ በጠራው ሰማይ ላይ የሚንከራተተውን እንደ ባዘቶ ጥጥ የተከመረና ብትንትን ያለ ነጭ ደመና እየተከተለች በራሷ የሃሳብ ጉም ላይ ተሳፍራ ከነፈች።

ከቦርሳዋ ውስጥ ያስቀመጠችውን የዶክተር ሌላውን ካርድ አውጥታ በጠርዙ ከንፈሯን መታ መታ እያደረገች ትኩር ብላ ስሙን ስታይ ቀይታ 'ዶክተር ሌላው ዲንሳ' አለች ድምጿን አሰምታ። ጣቱ ላይ ያየቻትን የጋብቻ ቀለበት ባይነ ህሊናዋ አሰበች። ሚስቱ ምን ትመስል ይሆን? ... ልጆችስ ይኖሩት ይሆን? ... ለቤተሰቦቹስ ምን አይነት ሰው ይሆን? መጀመሪያና ማለቂያ በሌለው ሀሳብ ስትናጥ ሰውነቷ ዛል አለ። ዓይኖቿም ቀስ በቀስ እየተከደኑ፣ ጥቅጥቅ ካለው የእንቅልፍ ደመና ውስጥ ሳታውቀው ገባች። የሌላው የቢዝነስ ካርድም እንቅልፍ በፈታቸው ጣቶቿ መሃል ተንሸራታ ግራ ደረቷ ላይ ወደቀች።

Brought to You by t.me/bookshelf99

፡ 8 ፡

ሌላው ቀኑ በቀጠሮ የተሞላና በሥራ የተጨናነቀ ሊሆን እንደሚችል እያሰበ በጠዋት ከቤት ወጣ። መንገዶቹ ገና በሰውና በመኪና ስላልተሞሉ ዘና ብሎ ለመንዳት ይመቻሉ። ፍንትው ባለው ጠዋት ፀሐይዋ፣ ወርቃማ ጨረሯን በለስላሳ ሙቀት አስጊጣ ማልዶ ከቤቱ ለወጣው ሁሉ ያለስለት ትቸራለች። ቀየት ሲል ደግሞ አርፍዶ የወጣውን በግለቷ መቅጣቷ አይቀርም። ዕለቱ ሐሙስ ነው ... ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሩብ ይላል የመኪናው ሰዓት። አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ ካለው የእናቱ ቤት ተነሥቶ ካርል አደባባይ ላይ ወደ ግራ አሳበረና ውስጥ ውስጡን ጠመዝማዛውን መንገድ ሲጨርስ፣ ቀለበት መንገዱ ከመግባቱ በፊት ካለው ካልዲስ ጎራ አለ። ማኪያቷቸውን ይወደዋል ... አሜሪካ የለመደውን ስታርባክስን ተክቶለታል። በተለይ ጠዋት ጠዋት ግቢው ጭር ስለሚል፣ ቀኑን በዕረፍት እንደመጀመር ያህል ይሰማዋል።

ደብል ማኪያቶ አዝዞ ከቤት ከመውጣቱ በፊት ሲያነብ ስለ ነበረው መጽሐፍ ማሰብ ጀመረ። ሌሊት ላይ ያለ ወትሮው እንቅልፍ እምቢ ብሎት ረዘም ያለ ሰዓት በማንበብ ነበር ያሳለፈው። ለረጅም ጊዜ መጨረስ ያቃተውን 'ዘ ሳይኮሎጂ ኦፍ ዲሲት' (የሐሰት ሥነልቦናዊ ሐተታ) የሚለውን መጽሐፍ አንብቦ መጨረሱ ደስ ብሎታል። መጽሐፉ ብዙ ጥናቶችን ተንተርሶ የተጻፈ በአስቂኝ ምሳሌዎችና በታዋቂ ሰዎች አባባሎች የተሞላ በውሸት ሥነልቦና ዙሪያ ለሁሉም አንባቢ እንዲሆን ተደርጎ የተጻፈ ነው።

ውሸት በሁሉም ባህሎችና ሰዎች ዘንድ የተጠላና የተወገዘ ድርጊት ቢሆንም፣ በዛው ልክ በስፋት የሚዘወተር ተግባር ነው ይላል። አፍቃሪ ከፍቅረኛው ... ነጋዴ ከደንበኛው ... የሃይማኖት መሪዎች ከምእመናኑ ጋር ይወሻሻሉ። ወላጅና ልጅ ... ሐኪምና ሕመምተኛ በየቀኑ ሊካድ በማይቻል ነጭና ጥቁር ውሸት የእውነትን መራራ ሥቃይ ሊያስታግሱ ይሞክራሉ። ውሸት እየረገሙ የሚያቅፏት፣ በሰው ላይ እየጠሏት የራስ ጉዳይ ሲሆን ግን የሚታገሥዋት ለማዳ አውሬ መስላ ታየችው።

Brought to You by t.me/bookshelf99

የቀረችውን ማኪያቶ ጨልጦ ሒሳብ ለመክፈል ከላከስ አደረገ። በመጽሐፉ የፊት ገጽ ላይ በተንሻፈፈ ጽሑፍ የተጻፈው ‘ውሽት ... ውሽት ...ውሽት’ የሚለው ከመጽሐፉ ዋና ርእስ ሥር ያለው ጽሑፍ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። በራሱና ለራሱ ሣቅ አለና ‘እስኪ ደግሞ ወደ ሆስፒታሉ ሄደን ... ብዙ የታመሙ ውሸቶችን እንስማ...’ ብሎ መኪናውን አስነሥቶ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ገሰገሰ።

ወደ ሆስፒታሉ እየቀረበ ሲመጣ፣ ዕቃ የሚኑ አይሱዙዎችና አህዮች፣ ሚኒባስ ታክሲዎችና ወደ የት እንደሚሄዱ እንኳ ለማወቅ የሚያስቸግሩ በሐሳብና በችግር የተዋጡ እግረኞች መንገዱን ሞልተውታል። አንዱ አንዱን ለመቅደም ሲሞክር በሚፈጠረው መዘጋጋት ሳቢያ ‘ጊዜ’ ሁሉንም ቀድሞ ያመልጣል። አንድ ወዳጁ ከብዙ ጊዜ በፊት ‘ኋላ ቀር ሕዝብ እርስ በርሱ ሲሽቀዳደም ጊዜ ራሱ ቀድሞ ያመልጠዋል። ጊዜ ያመለጠው ህዝብ ደግሞ ከኋላው ሌላ ሕዝብ ሊኖር አይችልምና ኋላ ቀርነቱን ማንም ሊወስድበትም ሆን ሊወስድለት አይችልም’ ያለው አባባል ትዝ አለው። ከሆስፒታሉ ጋር ድንበርተኛ የሆነው አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ሲደርስ ዳገታማዋ ቀጭን መንገድ በሰውና በመኪና ተዘጋግታ እሱም ረዘም ያለ ጊዜ ቆመ።

የቤተክርስቲያኑ ሃይማኖታዊ ድባብና በዙሪያው ያለው የመርካቶ ሸቀጡ ገንዘባዊ ጥድፊያ በመሃል በተሸነቀረው ሆስፒታል ላይ የጣሉት ተጽእኖ ገዝፎ ይታያል። የቤተክርስቲያኑ ተጽእኖ በሆስፒታሉ ስም ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በአጥሩላይ በቀይ ቀለም በተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችም ተከትቦ ይታያል። ከፊት ለፊት ያሉት የንግድ ቤቶችና የማያባራው የገበያ ትርክምክም ሁካታ ደግሞ የመርካቶን የጫጫታ ማኅተም በሆስፒታሉ የፊት ገጽ ላይ በማያሳስት ሁኔታ አኑሯል። እንደ ምንም ወደ ሆስፒታሉ መግቢያ ታጠፈና በሩ ሲከፈትለት ፈጠን ብሎ ከግቢው ጥልቅ አለ።

ከቆሙት መኪኖች መሃል ወደ አንድ ጥግ አካባቢ አቁሞ ወደ ሐኪሞች ቢሮ አቀና። በቅርብ ጊዜ በተሠሩት ሁለት ሕንጻዎች መካከል እየተራመደ እዚህና እዚያ በየውሃ ልኩና መሬቱ ላይ የተጉና የተቀመጡ ሕመምተኞችን እያለፈ ሄደ። ሁሉም በራሳቸው ዓለም የተጠመዱና ለግላቸው የሚያልገመጥሙ ምናልባትም በሚወስዱት መድኃኒት የደነዘዙ መስለው ይታያሉ። ጠዋት ሲሆን ደግሞ ፀሐይ ለመሞቅም ይመስላል በቀጥር በዛ ብለው ወር ወር ይላሉ። በስተቀኙ በኩል ያለው ሕንጻ የሴቶቹ መኝታ ክፍሎች የሚገኝበት ስለ ሆነም ይሆናል የሚታዩት አብዛኞቹ ሴት ሕመምተኞች ናቸው። የቀሸሸው ፒጃማቸው ገላቸውን እጅግም አለመሸፈኑ የረበሻቸውም አይመስሉም። የብዙዎቹ ጸጉር ተንጨባሮ ... ባዶ እግራቸውን ያለጫማ ወዲያ ወዲህ ሲንከላወሱ አማኑኤል የሌላ ዓለምና የሌላ ዘመን የአእምሮ ታማሚዎች ማጐሪያ እንጂ የሃያ አንደኛው ዘመን ሆስፒታል አይመስልም።

የሕመምተኞች ስም እንደ ወረፋቸው የሚጠራበትን መተላለፊያ ደጀኔ

Brought to You by t.me/bookshelf99

አልፎ ደረጃውን ከወጣ በኋላ፣ በሰው የተሞላችውን ጠባብ ኮሪደር 'ይቅርታ... ይቅርታ... አንድ ጊዜ...' እያለ በሰዉ መሃል አቁራርጦ አለፈ። ወደ ዩኒቨርስቲው የአእምሮ ሕክምና መምህራን ቢሮ ከመድረሱ በፊት፣ ሁሌም ያፍንጫን አቅም የሚፈታተነውን 'ሽንት ቤት' ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ፣ እንደ ተቀየመ ሰው ፊቱን አዙሮ አለፈ። በግራና በቀኝ የተለያዩ ተመላላሽ ሕመምተኞች የሚታከሙበትን ክፍሎች እንዳለፈ በስተግራ ያለው ቢሮ ገርበብ ብሎ ስለነበር ላመል ያህል አንኳኩቶ ገባ።

በየጠዋቱ ከሁሉ ቀድሞ የሚገባው ዶክተር ካሊድ ኮምፕዩተሩ ላይ ተጠምዷል። ሰላምታ ተለዋውጠው ትንሽ ካወሩ በኋላ ሰዉ እስኪመጣ ሻይ ለመጠጣት ከጐን በኩል ወዳለችው ካፊቴሪያ ሄዱ። በሆስፒታሉ ሠራተኞች የተጨናነቀችው ካፊ ውስጥ መቀመጫ ስላላገኙ ወጥተው በረንዳ ላይ ተቀመጡ። ከጣራው ላይ ካለው በረንዳ ላይ ዙርያ ገባው ሁሉ እስከ አጥር ግዶ ድረስ በግልጽ ይታያል። ያለ ምንም ከልካይ የፀሐይዋን መውጣት ማጣጣም ስለሚቻል ሉላሠው ብዙ ጊዜ ወጪ መቀመጡን ይመርጣል።

ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን፣ ለጠዋት ስብሰባው ወደ ቢሮ ተመለሱ። ጠባቧ ቢሮ በሕክምና ተማሪዎችና የአእምሮ ሕክምና ሠልጣኝ ዶክተሮች ታጭቃ ደረሱ። አንድ ሦስት የሚሆኑ አስተማሪ ስፔሻሊስት ሐኪሞችም በየወንበራቸው ተሠይመው የሪፖርቱን መጀመር ይጠባበቃሉ። ክፍሏ ሾጣጣና ጠባብ ዓይነት ስትሆን፣ የሐኪሞቹ የሥራ ጠረጴዛ፣ ቅርጽና ቀለማቸው የተዘበራረቀ ወንበሮች፣ የፋይል መደርደሪያ ቁም ሣጥኖችን፣ ካለፈ የምርምር ሥራ በተራረፉ የተበላሹ ኮምፒዩተሮችና በሌሎች ዕቃዎች ተጭበራ እንደ ጠገበ የድሃ ሆድ ተቀዝራለች።

በዶክተር ካሊድ መሪነት ስብሰባው ሲጀመር፣ አዳሪ የነበረው ሠልጣኝ ዶክተር በተረኝነቱ ሰዓት ስላያቸው አዳዲስ ሕመምተኞችና ሌሎች እክሎች ሪፖርቱን ባጭሩ አቀረበ። አንዳንድ ጥያቄዎች ከተሰነዘሩለት በኋላ ተማሪዎቹን ለማስተማር በማሰብ ባንዱ ሕመምተኛ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ውይይት ተደረገ። በሕመሙ ምክንያት ያደረገው ነገር አስደንጋጭና አስፈሪ ስለ ነበረ ሁሉም የቀረበውን ሪፖርት ጆሮአቸውን አቁመው ነበር የሰሙት። ሰልጣኙ ዶክተር ሪፖርቱን ቀጥሎ፣

"ሰውዬው ሕመሙ ሲጀምረው 'መሥሪያ ቤቴ ውስጥ ይከታተሉኛል ... ጎረቤቶቼንም ሲ አይ ኤ ቀጥሮአቸው ካሜራ ገጥመው ቀንና ሌሊት ያዩኛል' በማለት ነበር። ከዚህም የተነሣ እንቅልፍ መተኛት ጭራሽ አቁሞ እቤት መዋል ጀመረ። እየባሰበት ሲመጣ ደግሞ የውሻዬ ጆሮ ላይ ጨረር የሚረጭ መሣሪያ ተገጥሟል በማለት የሚወደውን ውሻ በመርዝ ገደሎ እጓሮው ቀበረው። ቤተሰቦቹ ተደናግጠው ወደ ጠበል ቢወስዱትም 'ደህና ነኝ ... አሻፈረኝ' ብሎ፣ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

"ትንሽ ሰነባብቶ ደግሞ ነገሩ እየባሰ ሲመጣ ሚስቱንና ሁለት ሕጻናት ልጆቹን

Brought to You by t.me/bookshelf99

መርዝ የሚረጭ መሣሪያ የእስራኤል የስለላ ድርጅት ደረታቸው ውስጥ ቀብሯል ማለት ጀመረ። በትናንትናው ዕለት ጠዋት ቤተሰቡን በጠቅላላ በገመድ አስሮና አንድ ክፍል ውስጥ ዘግቶባቸው ግቢ ውስጥ ሊቀብራቸው ጉድጓድ ሲቆፍር የተጠራጠሩ ጎረቤቶች ደረሱበት። ደግነቱ ባንዳቸውም ላይ አካላዊ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ደረሱበት እንጂ አሰቃቂ ነገር ነበር የሚሆነው። በመጀመሪያ ያካባቢው ሰዎችና ዘመዶቹ ተረባርበው ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል ወስደውት፣ ከዚያ ነው ተኝቶ እንዲታከም ወደዚህ የተላለፈው" ብሎ ሪፖርቱን ጨረሰ። ጥቂት ጥያቄዎችን ከጠየቁት በኋላ በሕመሙ ምንነትና ሊደረግለት ስለሚገቡ የሕክምና አማራጮች ከግማሽ ሰዓት በላይ ውይይት ተካሄደ።

የጠዋት ሪፖርቱ ሲያልቅ የሕመምተኞች ጉብኝት ጊዜ እስኪደርስ ሁሉም በየፊናው ከቢሮው ጋር ተበታተነ። አስተማሪ ሐኪሞቹ እዛው ቀርተው በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሰሞኑን ስለተደረጉ ለውጦች አንሥተው ሲያወሩ ቆዩ። ለአንድ ወር የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ ለመሥራት ከአውስትራሊያ የመጣች አንዲት አበሻ የአእምሮ ሐኪም የመጀመሪያ ቀኗ ስለነበር ስለ ሆስፒታሉ ሁኔታ ጥቂት አስረዱት። በሆስፒታሉ ውስጥ ቀደምት ከሆኑ ሳይኪያትሪስቶች አንዱ የሆነው ዶክተር ሰቦቃ ነው። ከሕመምተኛ የጉብኝት ሰዓት በፊት ሆስፒታሉን እያዞረ ሊያሳያቸው እሷንና ዶክተር ሌላሠውን ይዟቸው ወጣ።

እያንዳንዱን ክፍል እያዞረ ሆስፒታሉ ሲከፈት ከነበረው ታሪክ ጋር እያዋዛና እያጣቀሰ በመንገር አስጐበኛቸው። በመጨረሻም ቀድሞ የሠራተኞች ካፊቴርያ ከነበረውና ወደ ጥግ አካባቢ ካለ ጨለምለም ያለ ክፍል ገቡ።

"ቅድም የነበርንበት አዲሱ ሕንጻ ከመሠራቱ በፊት እንግዲህ ይኼ ነበር ካፌያችን። አሁን ሳየው የከተማ ዋሻ ነው የሚመስለኝ። ብዙ ታሪክ ያላት ቤት ናት" አለና እየሣቀ አስከትሏቸው ወደ ውስጥ ገባ። ጨለምና ቅዝቅዝ ያለ ክፍል ሲሆን፣ ዝቅ ያለ ጣራው የበለጠ ወደ ታች ይጫናል።

"እና አሁንም ይሠራበታል?" አለች፣ አዲሷ ዶክተር።

"እ ...ም ሥራ ይጠፋለታል ብለሽ ነው ዶክተር? ... የሕመምተኞችና የጠያቂዎች ካፌ ሆኗል። በየጠዋቱ ምን የመሰለ ቡና መሰለሽ የሚፈላው! አንዳንዴ እዚህ መጥቶ ቁጭ ማለት ደስ ይለኛል። ቅድም እንዳየሽው ሕመምተኛውና አስታማሚው ግቢው ውስጥ ነጻ ሆኖ ነው የሚኖረው። እንደ እናንተ አገር ባንድ ጠባብ ክፍል ተቀልፎባቸው አይውሉም። ቤተሰብም፣ ሕመምተኛም ሠራተኛውም ተረዳድቶና ተያይዞ ነው ሳይኪያትሪን የሚሠራው እዚህ እኛ አገር። ደሞዝ የሚከፈለው ለኛ ሆነ እንጂ ... ቁጥሯ ደሞዝ ከተባለ" ብሎ ሣቀ። ዶክተር ሰቦቃ ሲሥቅ ቦርጩና ጉንጩ አብሮ ስለሚፍነከነክ ሣቁ በራሱ አብሮት ያለን ሰው ሳይወድ በግድ ያሥቃል። ቡና እንዲጠጡ ስለ ተጋበዙ ከወደ ጥግ ቁጭ አሉ። የድሮ ትዝታዎቹን ሲያወራላቸው ቀየና አንድ አንድ ስኒ ቡና ጠጥተው ወጡ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

ዶክተር ሌላሠው የሕመምተኛ መጦብኛ ሰዓቱ ስለ ደረሰ ይቅርታ ጠይቀ ወደሚሠራበት የሕመምተኞች ክፍል ሲሄድ ሁለቱ ተያይዘው ወደ ሐኪሞቹ ቢሮ ተመለሱ። ጠጋ እያሉ ገንዘብና ሲጋራ የሚለምኑትን ህመምተኞች ሰላም እያለና እያዋራ ወደ ሕመምተኞች ክፍል ደረሰ። አማኑኤል በሳምንት አንድ ቀን ይመጣል። ክፍተኛ በሆነ የአእምሮ መቃወስ የታመሙ ሕመምተኞች ተኝተው ከሚታከሙበት ክፍል ውስጥ ነው የሚሠራው። ብዙ ሕመምተኞች በየጥጋ ጥጉና በየክፍሉ መግቢያ ደጃፍ ላይ ተቀምጠው እያወሩ ዐሐይ ይሞቃሉ። አንዳንዶቹ ሰብሰብ ብለው እጅግም የማይገባ ነገር እያወሩ ይሣሣቃሉ። ሌሎቹ ደግሞ ለብቻቸው ፈንጠር ብለው ከማይታዩ አጋሮቻቸው ጋር ይሟገታሉ፣ ወይ ያወጋሉ።

ሌላሠው በራፉ ላይ ቆም ብሎ "እንደምን አላችሁ?" ሲል ብዙዎቹ ሕመምተኞች ብድግ ብድግ እያሉ አጸፋ ሰላምታ ሰጡት። የተወሰኑት ከኋላ ተከትለውት ወደ ውስጥ ገብተው የነርሶቹ የሥራ ኬላ አካባቢ ትንሽ አንጣበቡና ወደ የመኝታቸው ሄደው ጋደም ጋደም አሉ። አልጋዎቹ እንደ ወታደር ካምፕ ተቀራርበው የተዘረጉ ናቸው። ባለው የቦታ ጥበት የተነሳ የሕመምተኞችን ደህንነትና የግል ነጻነት ያገናዘቡ አይደሉም።

ሕመምተኞች ወደ ሚታዩበት ክፍል ሲገባ ተማሪዎችና ሠልጣኝ ዶክተሮቹ በረድፍ ተደርድረው ሲጠብቁት ደረሰ። ተማሪዎቹ ቶሎ ቶሎ ስለሚለዋወጡ ስማቸውን ብቻ ሳይሆን መልካቸውንም ለማጥናት ያስቸግራል። ዛሬም አዲስ ዙር ተማሪዎች ናቸው ያሉት። የሕክምና፣ የነርሲንግ፣ የማማከርና የጤና መኮንንነት ተማሪዎች እየተፈራረቁ ስለሚመጡ ማን ማን መሆኑም ለማወቅ ይከብዳል። ሁለቱ የአእምሮ ሕክምና ሠልጣኝ ዶክተሮችንና የክፍሉን ቋሚ ነርሶች በስማቸው እየጠራ ሰላም ብሎ በተዘጋጀለት ወንበር ላይ ተሠየመ።

"እሺ ሰላም ነው... ታዲያስ? ዛሬም አዳዲስ ተማሪዎች ያሉን ይመስላል ... ሁላችሁም የሕክምና ተማሪዎች ናችሁ ወይስ?" ብሎ፣ ተራ በተራ ወደ ተማሪዎቹ ሲያማትር ሁሉም በአምንታ ራሳቸው ነቀነቁ። ሁሉም የመጨረሻ ዓመት የጥቁር አንበሳ ተማሪዎች መሆናቸውን ነገሩት። ለመተዋወቅ ያህል የያንዳንዳቸውን ስምና ሲጨርሱ ምን የሕክምና ዘርፍ ማጥናት እንደሚያስቡ ጠይቀ ትንሽ ካወራቸው በኋላ የቡድኑ መሪ ወደ ሆነችው ሠልጣኝ ዶክተር ዘወር ብሎ፣ "ዛሬ ብዙ የሚታዩ ሕመምተኞች አሉን እንዴ ዶክተር ምዕራፍ?" አለ፣ ከፊት ለፊቷ ወደ ተከመሩት ቻርቶች እያየ።

"እዚህ ወንዶቹ ክፍል ሦስት አዳዲስ ሕመምተኞችና ሁለት ደግሞ አስቸጋሪ የቀዩ ኬዞች አሉን። የምንችለውን ሁሉ ብናደርግም እየባሰባቸው ነው። አንዱ በተለይ ሌላ ሕመምተኛና ስታፍ ካልደበደብኩ ብሎ እያስቸገረ ነው። ትናንት ሌሊት መስኮት ሰብሮ በግድ ነው መርፌም የተወጋላቸው። ሌላው አዲስ ሕመምተኛ ግን ያ ጠዋት የተወያየንበት ኬዝ ነው" ብላ፣ እምታገላብጣቸው ቻርቶች ላይ ዓይኗን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ተክላ ዝም አለች ።

"ኦኬ ... ጥሩ ፤ በሴቶች በኩልስ ምን ያህል ሕመምተኞች አሉን?" አለ ፤ የሚኖረውን ጊዜና መታየት ያለባቸውን ሕመምተኞች ቁጥር ለማመጣጠን በማሰብ ።

"አዲስ ሕመምተኛ የለንም ፤ ግን ሁለት ኪዞች አሉ አብረን ብናያቸው ብሉን ያስብናቸው ። አንዱ ዝናሽ ናት" አለች ፤ የሚታዩትን ቻርቶች ከሌላኛው የአንደኛ ዓመት ሠልጣኝ ዶክተር ጋር እየተከፋፈሉ ። የአእምሮ ሕክምና ስፔሻላይዘሽን ሥልጠናው በአጠቃላይ የሚወስደው ሦስት ዓመት ነው ።

"ኦው ... ዝናሽን አይተሻት ነበር? እንዴት ናት? እንደውም ካባቷ ጋር ዛሬ ቀን ስምንት ሰዓት ላይ ቀጠሮ አለን አይደል ሲስተር?" አለ ፤ ዓይኑን በዶክተር ምዕራፍና በኃላፊ ነርሷ መካከል እያመላለሰ ።

"አዎን ... እንግዲህ አልቀርም እመጣለሁ ብለውኛል ከትናንት ወዲያ ። እሷም ብዙ ለውጥ አላት ። አሁንማ ወሯም እየገባ ነው መሰለኝ ፤ አልትራሳውንዱ የሚያሳየው እንደዛ ነው ። ሌላው ሜንቀት ግን እንግዲህ ድንገት ምጥ የመጣ እንደሆነ ነው ። በየሆስፒታሉ የኛን ሕመምተኞች ለመቀበል ያለው ችግር ሥቃይ ነው " አለች ፤ ሃላፊ ነርሷ ትንሽ በስጨት ባለ ድምጽ ።

"እኔም እሱን ሳስብ ነበር ። በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው ...ምን ማድረግ ይሻል ይሆን ታዲያ? ለመሆኑ የቤተሰቦቿ የኑሮ ሁኔታ እንዴት ነው?" አለ ፤ ፊቱ ላይ ግልጽ ያልሆነ ሜንቀት እየተነበበት ። ኃላፊ ነርሷ አሁንም ቀበል አድርጋ ፤

"አ-ዩ ዶክተር ሌላሠው ... አባቷ ድክም ያሉ ሽማግሌ ናቸው ። ለራሳቸውም በልመና ነው የሚተዳደሩት ። እንደሰማሁት ከሆነ የርሷንም ሁለት ሕፃናት ልጆችም የሚያሳድጉት እሳቸው ናቸው ። እንጃ ... የሆነ ነገር ካልተገኘ ፤ እንዲያው ምንም ተስፋ ያለውም አይመስለኝም" ስትል ፤ ክፍሉ በጨለምተኛ ደባብ ተሞላ ።

"የሆነ ነገርማ መደረግ መቻል አለበት ። ለማንኛውም እስኪ እሳቸውንም በኋላ አናግራቸዋለሁ ። እስኪ እዚህ ያሉንን ሕመምተኞች እንይና ወደ ሴቶች ክፍል ስንሄድ ስለርሷ እናወራለን" አለና ወደ ተማሪዎቹ ዞረ ። "ያው ለዛሬ አዲስ ስለሆናችሁ የሚደረገውን እዩ ። ጥያቄ ካላችሁ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ትችላላችሁ ። ከዚያ እነ ዶክተር ምዕራፍ ሁለት ሁለት ኪዞች ይሰጧችኋል ። በዚህ ሳምንት እነርሱን ኢንተርቪው አድርጋችሁ በሚቀጥለው ታቀርባላችሁ ። ምን ያህል ጊዜ ነው ከኛ ጋር የምትቆዩት?"

"ሁለት ሳምንት" አለ ፤ አንደኛው ተማሪ ፈጠን ብሎ ።

"ጥሩ ... በቃ የተቻለውን እናደርጋለና ። ያው እንደምታውቁት እዚህ ክፍል በተለይ የአእምሮ መቃወስና መረበሽ የደረሰባቸው የስኪዞፍሬንያ ህመምተኞች

Brought to You by t.me/bookshelf99

ናቸው ያሉን ። ስለዚህ ቢያንስ ያንን በደንብ ማወቅ ይጠበቅባችኋል ። አስቸጋሪና አዲስ የታመሙ ሕመምተኞችን ስታዩ ግን ከነ ዶክተር ምዕራፍ ጋር መሆን አለባችሁ ። ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብቻችሁ ሕመምተኛ እንዳታዩ ። ሁሉም ነገር ቀስ ተብሎ ነው ፣ ብዙ አትዳፈሩ ። ኦኬ ... ታዲያ የመጀመሪያው ን ከዝ ማነው የሚያቀርብልን?"

ያሉትን ሕመምተኞች ጉዳይና ሕክምናቸው ን እየተወያዩ መደረግ ያለበትን ነገር ወስነው ሲጨርሱ ፣ ሌሎች ጉዳዮችን ሲያወሩና የተነሡ ጥያቄዎችን ሲመልስ ቆዩ ። ከተረበሸና በከፍተኛ ደረጃ ከታመሙ ሕመምተኞች ጋር እንዴት ማውራት እንዳለባቸው በተግባር እያሳየና በገለጻ እያብራራ አስተማሪቸው ። ውይይቱን ሲጨርሱ የክፍሉን ነርሶች አመስግኖና ተሰናብቶ ወደ ሴቶቹ ክፍል ለመሄድ ተነሡ ። ወደ እዛው እየሄዱ ከዶክተር ሲራክ ጋር የምሳ ቀጠሮ ስለ ነበራቸው ቦታና ሰዓቱን ለማረጋገጥ ደወለለት ።

ወደ ሴቶቹ ክፍል ሲደርሱ ፣ ዝናሽ ከአንዲ ነርስ ጋር ቀማ ስታወራ አይቶ ባሳየችው ለውጥ ውስጡ ደስ አለው ። ሰውነቷ መለስ ያለ ይመስላል ። ጸጉሯ ታጥቦና ተስተካክሎ ሻሽ ጣል አድርጋበት ሌላ ሰው አስመስሏታል ። ባለቤቱ ንጹሕ የላከችላት የነፍሰ ጡር ቀሚስም ተስማምቷታል ። ሌላሠውን ስታይ ፈገግ ብላ ከበሩ ላይ ዞር አለችና ዓይኗን ሰበር አደረገች ። በደህናው ቀን ምን ዓይነት ሴት ትሆን ይሆን የሚል ጥያቄ በውስጡ አለፈ ።

"ታድያስ ዝናሽ ... እንዴት አለሽ?" አላት ፣ አጠገቧ ሲደርስ ።

"ደህና ነው ... ደህና... እየተሻለኝ ነው" አለች ፣ እንዳቀረቀረች ። የመድኃኒቱ የጐን ጉዳት ይመስላል ትንሽ እንቅስቃሴዋ ዘገም ፣ ስሜቷም ደብዘዝ ያለ መስሎ ታየው ። ከህመሙ አንጻር ለጊዜው የጐን ጉዳቱን መታገሡ የግድ መሆኑን አወቋል ።

"እንዴት ነው እንቅልፍስ ትተኛለሽ?" አላት ፣ አውንም ሁኔታዋን ለማጥናት እየሞከረ ።

"አምን ... ምንም አይል ..." አለች ፣ ጣቶቿን እያፍተለተለች ። ረጃጅምና ቀንጅዬ ጣቶች እንዳሏት አስተዋለ ።

"እሺ ጥሩ ነው ፤ በቃ ወደ ውስዋ ገብተን ፣ ተራሽ ሲደርስ እናይሻለን" ብሎ ፣ ትከሻዋን በማደፋፈር አይነት መታ መታ አደረገና ከሕክምና ቡድኑ ጋር ተከታትለው ገቡ ። ሌሎቹን ሕመምተኞች አይተው ሲጨርሱ ነበር ዝናሽን ያዩዋት ።

ሻሿን ፊትታ እንደ አንገት ልብስ ጣል አድርጋ ከፊት ለፊት ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠች ። የእግር ጣት ጥፍሮቿ ተቁርጠው ፣ ቀለል ያለ ጫማ ተጫምታ ስትታይ በባዶ እግሯ ስትዳክር የከረመች አትመስልም ። ጠቁሮና ገርጥቶ የነበረው

Brought to You by t.me/bookshelf99

መልኳ መመለስ ሲጀምር፣ የሚያምር የጥቁር ጠይም ቀለሟ መውጣት ጀምሯል። የስሜቷ መለከንና የአስተሳሰቧ መረጋጋት፣ መልኳንና የሴትነት ወዘናዋን መልሶት ደርባባ ነፍሰ ጡር አስመስሏታል። በጫማዋ መሬቱን እየጠበጠበች፣ አገጯን ባስደገፈችበት እጁ ሞንቅላቷን እንደ ተሸከመች ሰውነቷን አስቀምጣላቸው በሐሳብ ሞልጥ ብላ ሩቅ ሄዳለች።

የተጋገረውን የጸጥታ በረዶ ለመስበር በማሰብ፣ "እንዴት ነው ... መድኃኒቱ ተስማማሽ ዝናሽ?"

ከእንቅልፏ እንደባነነ ደንገጥ ብላ፣ "እ ... ጥ...ጥሩ ነው መሰለኝ፣ ያው ነው። ድክም ይለኛል ግን፣ መድኃኒቱ ነው መሰል ፍዝዝ ያደርገኛል። እነርሱም ደግሞ ተይ ኪኒኑን አትውሰጂ ይቅርብሽ ሊገድሉሽ ነው ይሉኛል። እስኪ ተዉ ... ኡፍ" አለችና በስጨት በማለት እጁን ስታወናጭፍ፣

"እነማናቸው እነሱ?" አለ፣ ፊቱን ቅጭም አድርጎ።

"ያው የልጁ ባለቤቶች ናቸዋ። ልጁን ሊገድሉብን ነው ኪኒንና መርፌ የሚሰጡሽ ይላሉ። ሌሊት መጥተው ደግሞ ... ኡፍ ...ፍ ... አይሰማችሁም ሲያንሾካሽኩ። ግን መድኃኒቱ ሰው ይገድላል እንዴ?" ትክ ብላ ስታየው መረበሿን በመረዳት እንዴት ሊያስረዳት እንደሚችል ትንሽ አሰበ።

"እየውልሽ ዝናሽ የምንሰጥሽ መድኃኒት ላንቺም ሆነ ለጽንሱ ጤንነት በጣም አስፈላጊ ነው። አሁን ሞንቅላትሽ ውስጥ እየሰማሽ ያለው ድምፅና ሐሳብ እንደሚረብሽሽ ይገባኛል። ደግሞ ብዙ ጊዜ ጥሩ ምክርም አይሰጡሽም አይደል?"

"ኡፍ...ፍ ምን ጥሩ ምክር አለ ብለህ ነው። ቆይ ዝም እንዲሉ ማድረጊያ ነገር የለም እንዴ? ምነው አሁንስ ... እነርሱ ያለ እኔም ሰው አላዩም እንዴ? ተውኝ ካልኳቸውማ በቃ የባሰ ጆሮዬ እስኪደነቁር ይጮሁብኛል፤ ደግሞ ያስፈራሉኛል። ትንሽም ጋብ የሚልልኝ ወይ ስተኛ ወይ መድኃኒቱን እንደ ወሰድኩ አካባቢ ብቻ ነው" ብላ፣ ርብሽ ያለ ፊቷን በጆቿ ሸፍና ዝም አለች።

"እስኪ መድኃኒቱንም እናስተካክልልሻለን። ድምፁ ሲረብሽሽ ደግሞ ለነሲስተር ንገሪያቸው። ድምፁን ከጆሮሽ ላይ የሚያጠፋ መድኃኒት ይሰጡሻል። ሁለት ሳምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጥ ነው ያሳየሽው። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደግሞ የበለጠ ደህና ትሆኛለሽ። ስለዚህ አይዞሽ። ሌላስ ምን ችግር አለ?" አለ፣ ሥቃዩዋ እያሳዘነው።

"እኔ እንጃ፤ በቃ ድምፁን ካጠፉችሁልኝ ሌላው ደህና ነው መሰለኝ። የማያደክምና የማያፈዝ መድኃኒትስ የለም እንዴ? በፊትም እኮ ሻል ሲለኝ መድኃኒቱን የማቆመው ለዚህ ነው" አለች፣ በከፊል ቀና ብላ ሁሉንም በዐይኗ ገረፍ እያደረገች።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"እስኪ ከነዶክተር ምዕራፍ ጋር ተነጋግረን የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለና። ቤተሰብስ ይመጣሉ ሊያዩሽ?" አለ፣ ርዕሱን መቀየር ስለፈለገ። እግረ መንገዱንም ከቤተሰብ ጋር ያለውን ሁኔታ ለመቃኘትና ከአባቷ ጋር ያለውን የከሰዓት በኋላ ቀጠሮውንም ታውቅ አታውቅ መሆኑን ለማወቅ ፈልጎ።

"ምን ቤተሰብ አለና ... አባቴ ነው ያለው ... እሱም አርጅቷል ... ልመና ነው የሚውለው ... አንድ ሁለት ጊዜ መጥቶ ነበር መሰለኝ ..." ብላ፣ ትክዝ አለች።

"አባትሽ ዛሬ በኋላ ይመጣሉ መሰለኝ። አይዞሽ እኛም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። እስኪ የቀረውን ደግሞ ከሰዓት በኋላ እናወራለን" ሲላት፣ ምንም እንዳልሰማ ዝም ብላ መሬቱን መቀርቀሯን ቀጠለች።

"ፅንሱስ እንዴት ነው? ወርሽም እየገባ ነው አይደል?" ሲል፣ ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ አሁንም ዝም አለች። ወደ በሩ ደጋግማ ስታይ በሰዉ ብዛት ተጨንቃ ሊሆን እንድሚችል ገምቶ፣ "በቃ እሺ ከሰዓት በኋላ አባትሽን ካዋራሁ በኋላ አናግርሻለሁ። ጥያቄ ከሌለሽ አሁን መሄድ ትችያለሽ። ችግር ካለ ግን ለነሲስተር ንገሪያቸው እሺ?" ብሎ፣ እጁን ሲዘርጋላት ላመል ያህል ጨብጣው እንዳገነበሰች ወጣች። እሷ እንደ ወጣች ሠልጣኝ ዶክተሮቹን ጨምሮ ከተማሪዎቹ ጀምሮ በተራና በየደረጃው ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ዝናሽ ሕመም ትምህርታዊ ውይይት ጀመሩ።

"እሺ ስለ ዝናሽ ዶክተር በነገረችን ታሪክና ከራሷም በሰማነው መሠረት ሕመሟ ምን ይመስላችኋል?" አለ፣ ወደ ተማሪዎቹ እያየ። አጠር ቀጠን ያለች ከፊት ለፊቱ የተቀመጠች ተማሪ ፈጠን ብላ፣

"ክሮኒክ ፓራኖይድ ስኪዞፍሬንያ ..." አለች፣ ርግጠኛ በሆነ ቁርጥያለ ድምፅ።

"ስኪዞፍሬንያ ምን እንደሆነና ያንን ለማለት ያስቻሉሽን፣ ዝናሽ ላይ ያሉትን የሕመም ምልክቶች ልትነግሪን ትችያለሽ?" ሲላት፣ ጥያቄውን ስላልጠበቀች ትላልቅ ዓይኖቿ ከነሪያቸው በከፊል ወጥተው በፊቷ ላይ ተንከባለሉ። ጥቂት ካሰበች በኋላ፣

"እ...ም ክሮኒክ የምንለው ያው ካንድ ዓመት በላይ በመታመሟ ሲሆን ... እም... ያው ከፍተኛ የመጠራጠርና ያለማመን ስሜት ስላላት ፓራኖይድ ዓይነቱ ነው ሊባል ይችላል። ድምፅ መስማቷ፣ የተለያዩ ከእውነታ የወጡ አስተሳሰቦችና እምነቶችም ስላሉዋት ስኪዞፍሬንያ ይመስለኛል ሕመሟ" ስትል፣ የእንግሊዝኛ አነጋገር ችሎታዋ ብቻ ሳይሆን ስለ ሕመሙም ያላት ግልጽ መረዳት ደስ ብሎት፣

"በጣም ጥሩ ... ሌላስ ..." አለ፣ ወደ ሌሎቹ ተማሪዎች ዞሮ። ሁሉም ዝም ሲሉ ወደ አንደኛ ዓመት ሠልጣኝ ሐኪሙ ዞር አለ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ከዛ በተጨማሪም የባሕርይ መረበሽና የንግግር መዘበራረቅን ማሳየትንም ይጨምራል። የአእምሮ መረበሽን የሚያመጡ እንደ አደንዛዥ ዕፆችና የተለያዩ አካላዊ ሕመሞች እንደ መንስኤ ካሉ ግን ሕመሙን በርግጠኝነት ስኪዞፍሬንያ ማለት አይቻልም። ዝናሽ ግን ሱስ ቢኖርባትም፣ ከሕመሙ በኋላ የጀመረቻቸው ስለሆኑ ሕመሙን ሊያባብሱት ይችላሉ እንጂ እንደ መንስኤ ልናያቸው አንችልም። ሌላ ይህ ነው የሚባል የአእምሮ መረበሽን ሊያመጣ የሚችል አካላዊ የሆነ ሜዲካል ችግር ያላት አይመስለኝም" አለና ተስተካክሎ ተቀመጠ።

ሌላሠው ከሱ ቀበል አድርጎ፣ "ልክ ነው ... በነገራችን ላይ ስኪዞፍሬንያ የምንለው በአብዛኛው በተለምዶ 'እብደት' የምንለውን ችግር ነው። ብዙ ጊዜ በየመንገዱ የምናያቸው ጨርቃቸውን የጣሉ 'እብዶች' የዚህ ሕመም ተጠቂዎች ናቸው። የቃሉ ጥሬ ትርጉም 'የተከፋፈለ አእምሮ' እንደ ማለት ነው። ይህም ሕመሙ የውጭውን ነባራዊ እውነታና በውስጣችን የሚገኘውን የሐሳብ ዓለም አጣጥሞና አስማምቶ ለመኖር አለመቻልን ስለሚፈጥር ነው። ያልሆኑ ነገሮችን ማመንና የሆኑትን መካድ ... ያልተፈጠሩ ነገሮችን ማየትና መስማትን ... በዚህም የውስጥ መረበሽየተነሣ ... የንግግር፣ የባሕርይና የስሜት መዛባቶችም ይፈጠራሉ። እሺ ጥሩ ... መንስኤውስ ምንድነው?" በማለት፣ ተማሪዎቹን ሲያይ ሁሉም ዝም ዝም ብለው ዓይናቸውን ሲያሸሹ ወደ ዶክተር ምዕራፍ ዞር አለ።

የያዘችውን የሕመምተኛ ካርድ እየዘጋች ጉሮሮዋን ጠረግረግ አድርጋ፣ "እርግጠኛ የሆነ አንድ መንስኤ ተብሎ የሚባል ነገር እስካሁን አልተገኘም። ግን ብዙ መላምቶች አሉ። ዋና ዋናዎቹን ከሕመሙ መከሰት ጋር የሚያያዙ ነገሮች በአጠቃላይ በሦስት ልንከፍላቸው እንችላለን" አለችና ያሰበችው የጠፋባት ይመስል የያዘችውን እስክርቢቶ እያፍተለተለች ትንሽ አሰብ አድርጋ፣ "ይህም ለሕመሙ የሚያጋልጡ፣ ሕመሙን የሚቀሰቅሱና የሚያባብሱ ነገሮች ብለን እንከፋፍላቸዋለን። ማንም ሰው ለሕመሙ መቶ በመቶ ያልተጋለጠ ነው ማለት ባይቻልም አንዳንድ ሰዎች ግን በቅርብ ዘመዶቻቸው ወይም በቤተሰብ ውስጥ ሕመሙ ያለበት ሰው ካለ ከሌላው ሰው የበለጠ የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ። እም...ም በተጨማሪም አንዳንድ የሰብእና አወቃቀሮችም የቅድመ ስኪዞፍሬንያ ምልክት ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያ ውጪ ያሉት ቲዎሪዎች ግን ገና የሩቅ መላምቶች ይመስሉኛል።

"በሌላ በኩል ደግሞ ከአቅም በላይ የሆነ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና ሲኖር፣ በለጋ ዕድሜ ሱስ በሚያሲዙ አደገኛ ዕፆች መጠመድ፣ ከፍተኛ በሆነ አካላዊ አደጋ ሳቢያ የጭንቅላት መጐዳት ሲደርስና የመሳሰሉት ደግሞ ሕመሙ እንዲከሰት አስተዋጽኦ ሊኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም ሌሎች ማኅበራዊና የግል ሕይወት ጫናዎችና መድኃኒቱን በትክክል አለመከታተልና የመሳሰሉ ነገሮች ደግሞ ሕመሙ ለመባባሱና ላለመሻሉ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ..." ብላ፣ ሐሳብ እንዳለቀባት ድንገት ዝም አለች፣

Brought to You by t.me/bookshelf99

"በጣም ጥሩ ነው ። ሌላው እይታ ደግሞ በአንገላችን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኬሚካሎች መዛባት ይሆናል የሚለው ነው ። ለምሳሌ ዶፓሚን የሚባለው ኬሚካል ተዛብቶ ባንዳንድ ያንገላችን ክፍሎች ከሚገባው በላይ ሊበዛ ወይም ሊያንስ ይችላል የሚለው መላ ምት አለ ። የምንሰጣቸው መድኃኒቶች በአብዛኛው ይህንን መዛባት ነው የሚያስተካክሉት ። ሌሎች ቲዎሪዎች ደግሞ እንደ ሴሮቶኒንና ግሉታሜት የመሳሰሉ በአንገል ውስጥ ያሉ ሌሎች ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች መዛባት ነው ይላሉ ። ለዚህ ነው ለምሳሌ የተለያዩ አደንዛዥ ዕፆችን በከፍተኛ ደረጃ የሚወስዱ ሰዎች የአንገላቸው ውስጥ ኬሚካሎች ሲዛቡ ፍጹም ስኪዞፍረንያ ብለን ከምንጠራው የአእምሮ መረበሽ ሕመም ተመሳሳይ ምልክቶችን የሚያሳዩት" ብሎ ፣ የተለያዩ ቲዎሪዎችን ከነመነሻ ሐሳባቸው ጋር በሰፊው ካሰረዳቸው በኋላ ፣ ጥያቄዎቻቸውን ሲመልስ ቆየ ። ሰዓቱን አይቶ ለመውጣት ሲል አንደኛዋ ተማሪ እጇን አውጥታ ጥያቄ አቀረበች ።

"ብዙ ጊዜ ባጠቃላይ የአእምሮ ሕመሞች በተለይ ደግሞ ስኪዞፍረኒያ የምንለው የአእምሮ መቃወስ ሲፈጠር መንፈሳዊ መንስኤ አለው ተብሎ ነው የሚታመነው ... በተለይ በእኛ ባህል ውስጥ ። ከአእምሮ ሕክምና ሳይንስ አንጻር ስለ መንፈሳዊ ነገር ያለው እይታ ምንድን ነው?" ብላ ፣ ባነሣችው ሐሳብ ዙሪያ የተነሳ የጋለ ውይይትና ክርክር ሲያደርጉ ቆዩ ።

በመጨረሻም እሱ ነገሩን ሲያጠቃልለው ፣ "እ ...ም እንግዲህ ምን ያህሉ መንፈሳዊ ነው ፣ ምን ያህሉ አካላዊ ነው ፣ የሚለው ሁሌም አከራካሪ ነገር ነው ። ባንድ በኩል የጉበትና የጨጓራን ህመም እንደ ተፈጥሮአዊና አካላዊ ሕመም አድርጎ መቀበል ለብዙ ሰው ቀላል ነው ። የአእምሮ ሕመም ሲሆን ግን አንጎልም የሰውነት አካል ስለሆነ በተመሳሳይ መንገድ ሊታመም ይችላል ብሎ ማመን የሚቸግራቸው ብዙ ሰዎች አሉ ። ብዙ ጊዜ በሃይማኖት አካባቢ ያሉ ሰዎች አካላዊ ገጽታውን ለመቀበል ይቸገራሉ ።

"በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው የአእምሮ ሕክምናና የሥነልቦና ሳይንሶችን ሞልቶ ያለው የሕይወት እይታ ወይም ንጽረተ ዓለም የመንፈሳዊውን ዓለም መኖር አይቀበልም ። በዚህ ቁሳዊ በሆነ የፍልስፍና እይታ የፈጣሪን መኖር ጨምሮ ሰይጣንና ጋኔን የሚባል ነገር አለ ብሎ ማመንም እንደ ሞኝነት ነው የሚታየው ። ሰዎች በርኩስ መንፈስ ተይዘው ባሕርያቸውና ማንነታቸው ይቀየራል የሚለውን እይታ እንደ ከንቱ ያረጀ ያፈጀ ልማድ ነው የሚወስዱት ። የሰውን መንፈሳዊነት የሚቀበሉበት ሁኔታ ቢኖርም ሰው ውስጥ ተጀምሮ ሰው ውስጥ እንደሚያልቅ እውነታ ወይም አንድ የማንነት መገለጫ አድርገው ብቻ ነው የሚወስዱት ። መንፈሳዊውን ዓለምና እውነታ መቀበል በማይቻልበት ሁኔታ ደግሞ ችግሩንም ሆነ መፍትሔውን መንፈሳዊ አድርጎ መውሰድ ራሱ ኢሳይንሳዊ ተደርጎ ነው የሚገመተው ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"በእኔ እይታ ግን ... ሰው ሁለቱም ካምፖች ከሚሉት በላይ የተወሳሰበና ምስጢራዊ የሆነ ፍጥረት ይመስለኛል። እኔ ባለኝ ልምድ በመንፈሳዊ እገዛ ፈጽመው የተረዱም የተገዱም ሰዎች አውቃለሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ በዘመናዊው ቁስ መር ሕክምናም የተረዱም የተገዱም ሰዎች አሉ። አሁን የደረስኩበት መረዳት፣ ሰው አንድ ስለሆነ ሳናከፋፍልም ሳናበላልጥም በሁለቱም እውነታዎች ሊታይና ሊረዳ ይገባል ነው። በመንፈሳዊውም ሆነ በአካላዊው መፍትሔዎች በኩል ያሉትን ጥሩ ነገሮች ክፍት በሆነ ልቦና መጠቀም ያስፈልጋል ባይ ነኝ። በመካከል በተፈጠረው ገደል ላይ ድልድይ መሥራት የሚሻል ይመስለኛል። አለበለዚያ ከሁሉም በላይ የሚጐዳው ሕመምተኛው ነው" አለ፣ በረጅሙ ተንፍሶ ሰዓቱን እያየ።

"ኦህ ማይ ... ሰዓቱ እንዴት ሄዷል ባካችሁ። ለምሳ ቀጠሮዬ ሳላረፍድም አልቀረሁ። ለማንኛውም ይሄ ብዙ አነጋጋሪም አከራካሪም ጉዳይ ነው። ስለዚህ በሚቀጥለው ሳምንት እንቀጥለዋለን።" አለና ወደ ሃላፊ ነርሷ እያየ፣ "ሲስተርዬ፣ ያው ስምንት ሰዓት ላይ እመጣለሁ። በሉ ቻው" አለና እጁን ለሰላምታ አውለብልቦ እየተጣደፈ ትቷቸው ወጣ።

Brought to You by t.me/bookshelf99